የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን አካባቢ የትራንስፖርት ባለሥልጣን

የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ

2020 - 2023

የዋሽንግተን ሜቶርፖሊታን አካባቢ የትራንስፖርት ባለሥልጣን (ሜትሮ) ትራንስፖርት-ተኮር በሆነ የህዝብ ተሳትፎ፣ ተደራሽነት እና ግንኙነት መሪ ለመሆን ይጥራል። የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ (PPP) ደንበኞች እና የማህበረሰብ ዓባላት በታቀዱ ፕሮጀክቶች ዙሪያ ከፍተኛ ጥራት ያለው መረጃ፣ የግንኙነት እና የግብረመልስ ዕድሎችን ለመቀበል እና የፌዴራል ግዴታዎችን ለመወጣት እንደ መመሪያ መሳሪያ ሆኖ በማገልገል ለሕዝብ ተሳትፎ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።

ምዕራፍ 1: - የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ መርሆዎች

መመሪያ መርሆች.. 1-2

የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ግቦች እና ዓላማዎች.. 3

ህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ የመጀመሪያ ሂደት ቁልፍ ግኝቶች 4

የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች 5

የአገልግሎት ክልል ስነ-ህዝብ ስብጥር 6-7

የሜትሮ ደንበኞች ስነ-ህዝብ ስብጥር 8

የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ግምገማ 9

መዕራፍ 2: ለህዝብ ግንኙነት እና ለታቀዱ ፕሮጀክቶች ተደራሽነት መመሪያዎች

የፕሮጀክት አጀማሬ 12-14

የግንኙነት ዕቅድ ሂደት 15-21

የግንኙንት ዕቅድ አፈጻጸም 22

ቁጥጥር፣ ክትትል እና ሪፖርት ማድረግ 23

መዕራፍ 3: የ 2017-2020 PPP ግምገማ

የፕሮጀክቱ ዓብይ ጉዳዮች 25-27

የህዝብ ተሳትፎ አስተዳደር ሥርዓት እና በየሦስት ዓመቱ የ PPP የአፈፃፀም መለኪያ ሪፖርት 28-29

የህዝብ አስተያየትን መጠየቅ.. 30

የማህበረሰብ ድርጅት ተሳትፎ.. 31

የቋንቋ ተደራሽነት 32-33

የሜትሮ የፍትሃዊነት የሥራ ቡድን ጅመራ 34

ሥልጠና.. 35

የሠራተኞች አወቃቀር 36

ከአዲሱ ሁኔታ ጋር መለማመድ 37

አባሪዎች (እያንዳንዱ በ PDF ፋይሎች ቀርበዋል)

አባሪ ሀ: የፌደራል እና የሜትሮ ኮምፓክት (Compact) ማስፈርቶች ግምግማ

አባሪ ለ: የስነo-ህዝብ መለያ መረጃ

አባሪ ሐ: የአቻ ትራንዚት ኤጀንሲ ግምገማ

አባሪ መ: የተደራሽነት እንቅስቃሴ ዝርዝር

ምዕራፍ አንድ: የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ መርሆዎች

የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ስለ ፖሊሲው እና አገልግሎቶቹ ምክንያታዊ፣ ሁሉን ያካተተ እና በትብብር ሂደት በሚካሄድ የተሳፋሪዎች እና ተሳፋሪ ያልሆኑ ሰዎችን አስተያየት ባካተተ መርሆ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

ሜትሮ የፌዴራል ድጋፍ ተቀባይ እንደመሆኑ እና በ 1964 የሲቪል መብቶች ሕግ አንቀጽ 6 መሠረት በዕቅዱና በመርሃ ግብሩ እንቅስቃሴዎች አናሳ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋስ ችሎታቸው አነስተኛ የሆነ (LEP) ህዝቦችን ለማሳተፍ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ለፌዴራል ትራንስፖርት አስተዳደር (FTA)ማቅረብ አለበት፡፡ የፌዴራል ድጋፍ ተቀባዮች "የተወሰኑ የሕዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች እንዴት፣ መቼ እና ምን ያህል ጊዜ መከናወን አለባቸው" የሚለውን ለመወሰን "ሰፊ የሃሳብ ነጻነት" አላቸው፣ ሆኖም፣ እነዚህ ውሳኔዎች በህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ምስረታ በተገኙ ስነ-ህዝባዊ ትንተና እና በግብዓት ውጤቶች (ለምሳሌ፣ ተደራሽነት እና ጥራት ያለው ጥናት) መደገፍ አለባቸው።

የ WMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ (PPP) ለመጀመሪያ ጊዜ በ 2013 እ.ኤ.አ. የተቋቋመው በተለያዩ ዲፓርትመንቶች ቡድን የተመራ የአንድ ዓመት ብዙ ደረጃ ሂደት ነው። አጠቃላይ የማቋቋም ሂደቱ የፌዴራል መስፈርቶች ግምገማን፣ በሀገሪቱ ዙሪያ ያሉ አስር የትራንስፖርት ኤጀንሲዎች ምርጥ አሠራር ግምገማ፣ የሠራተኞች እና የቦርድ ዓባል ቡድን ቃለ መጠይቆች፣ አንቀጽ 6 ን የሚያገለግሉ ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ሌሎች በ WMATA አገልግሎት አካባቢ ያሉ ለተደራሽነት አስቸጋሪ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካትታል። የ WMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ (PPP) እ.ኤ.አ. በመስከረም ወር 2014 በ WMATA የቦርድ ድሬክተሮች እና በጥር 2015 እ.ኤ.አ. በፌዴራል ትራንስፖርት አስተዳደር ፀድቋል።

ምንም እንኳን ይህ ዕቅድ የአንቀጽ 6 መስፈርቶችን ለማሟላት የተሠራ ቢሆንም፣ ማዕቀፉ በሁሉም በባለሥልጣኑ በታቀዱ የግንኙነት ጥረቶች "ተፈላጊ" የሆኑ ወይም ያልሆኑ ፕሮጀክቶች አካባቢ በሥራ ላይ እንዲውል የታቀደ ነው። በዚህ ዕቅድ ውስጥ የተካተቱት የሜትሮ የህዝብ ግንኙነት እና ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ውስንነቶች እና/ወይም ተሳታፊነታቸውን ሊገድቡ የሚችሉ እንቅፋቶች ላሏቸው ቡድኖች ተደራሽነትን የሚያሻሽሉ ስልቶችን በማዘጋጀትና በመጠቀም ለሁሉም ሰዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

ይህ የ 2020-2023 የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ እትም የሜትሮን በህዝብ ግንኙነት እና ተደራሽነት፣ የአዲሱ አስተዳደር መመሪያን፣ ስኬቶችን እና የተገኙ ትምህርቶችን እና በድርጅታዊ መዋቅር ላይ የተደረጉ ለውጦችን ጨምሮ እንዲያንጸባርቅ ተደርጎ ተሻሽሏል።

በዓለም ዙሪያ የህዝብ ተሳትፎ አሠራርን በማስተዋወቅና በማሻሻል ረገድ መሪ የሆነው ዓለም አቀፉ የህዝብ ተሳትፎ ማኅበር (IAP2) ተጽዕኖ ሊደርስባቸው በሚችሉ ሰዎች እና አካላት ፍላጎቶች እና ሥጋቶች የሚያንፀባርቁ የተሻሉ ውሳኔዎችን ለመፈጸም የሚረዳ የ IAP2 ዋና እሴቶችን አዘጋጅቷል። አብዛኞዎቹ እነዚህ ዋና እሴቶች ከታች የተጠቀሱትን ጨምሮ ሜትሮ ለሁሉም የህዝብ ግንኙነት እና ተሳትፎ ያለውን ዓላማዎች ያንፀባርቃሉ፡

- የህዝብ ተሳትፎ በውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው የሚችል ወይም የውሳኔ ፍላጎት ያላቸውን በመፈለግ ተሳትፏቸውን ያመቻቻል።
- የህዝብ ተሳትፎ ተሳታፊዎች በንድፉ እንዴት እንደሚሳተፉ አስተያየት ይጠይቃል።
- የህዝብ ተሳትፎ ተሳታፊዎች ትርጉም ባለው መንገድ ለመሳተፍ የሚፈልጉትን መረጃ ይሰጣል።
- የህዝብ ተሳትፎ የተሳታፊዎች አስተያየት ውሳኔው ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንዳደረሰ ይገልጻል።

እነዚህን ዋና እሴቶች በመከተል እና PPP በተፈጠረበት ጊዜ ጠንካራ በሆነ የማጣሪያ ሂደት አማካኝነት ሜትሮ የሥልጣኑን ፍልስፍና ለእኩልነት እና ለምርጥ የህዝብ አገልግሎት ያለውን ትልቅ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ መመሪያዎችን፣ ግቦችን እና ዓላማዎችን ፈጥሯል፡፡ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዱን ለሚያነሳሱ ፕሮጀክቶች እነዚህ መርሆዎችን መከተል አለባቸው፡፡

የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ግቦች እና ዓላማዎች

ግብ አንድ: ያካተተ

በህዝብ ተሳትፎ ሂደት ተጽዕኖ ሊደርስባቸው የሚችሉትን የሁሉንም ማህበረሰቦች ተሳትፎ በንቃት ማመቻቸት።

ግቦች:

- ሜትሮ የሚያገለግላቸው ህብረተሰቦችን፣ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑ (LEP/NEP)፣ ዝቅተኛ ትምህርት ያላቸው እና የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ፣ ፍላጎቶች የሚያሟሉ የመገግባቢያ ቁሳቁሶችን እና የትርጉም አገልግሎቶችን ማቅረብ።
- አናሳዎች እና የ LEP ማህበረሰቦች በስብሰባ ዝግጅቶች እና በመገናኛ ቁሳቁሶች በሄራቸውን፣ ዘራቸውን እና ቋንቋዎቻቸው ሲንፀባርቁ ማየታቸውን ማረጋገጥ።
- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ማህበረሰቦች ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ዘዴዎችን ማካተት።
- ሌሎች እንቅፋቶችን (ለምሳሌ፣ አካላዊ፣ ፋይናንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ባህላዊ) ዕውቅና እና መፍትሄ የሚሰጡ በርካታ የተሳትፎ ዘዴዎችን ማካተት።

ግብ ሁለት: ተባባሪ

በፕሮጀክቱ ዕቅድ እና ሂደት ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ መሥራት።

ዓላማዎች:

- ለትርፍ ያልተቋቋሙ፣ ባህላዊ ቡድኖች እና ተከራይ/አጎራባች ድርጅቶችን ጨምሮ ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ዘላቂ እና ትርጉም ያለው ግንኙነቶችን ማጠናከር።
- ውሳኔ አሰጣጥ ለማሳወቅ የቅድሚያ ግብዓት ማግኘት።
- ህብረተሰቡ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ግብረመልስ መስጠት እንዲችል፣ ለመረዳት የማያስቸግር ዝርዝር መረጃን በጊዜ ማስተላለፍ።
- ከሁሉም የህብረተሰብ ዓባላት ግብረመልስ የሚያመቻቹ ተደራሽ እና ልዩ ልዩ ስልቶችን መጠቀም።
- የአከባቢው የክልል አስተዳደር ባልደረባዎች እና የሜትሮ ቦርድ ዓባላት ማህበረሰቦቻቸው ተፅእኖ በሚደርስባቸው ጊዜ በተደራሽነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተሳተፉ እና የተካተቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

ግብ ሶስት: ምላሽ ሰጭ

መተማመንን ለመጨመር የሕዝቡን ግብረመልስ በንቃት ከውጤቶች ጋር ያገናኙ።

ዓላማዎች:

- የተሳትፎ ዝመናዎችን እና ውጤቶችን በቀጥታ ለተሳታፊዎች በጊዜው ማቅረብ።
- የመጨረሻ አስተያየቶች ሲዘጋጁ የህዝብ አስተያየት እንዴት ሥራ ላይ እንደዋለ በግልፅ ማስረዳት።
- በአጠቃላይ በተፈላጊ ወይም አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ለህዝብ አስተያየት መስጫ ዕድሎችን መፍጠር።

ግብ አራት: ወጥነት ያለው

ከሕዝብ ተሳትፎ ዕቅድ የቀረቡ መመሪያዎች በመላው ሜትሮ መከተላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማዎች:

- በሜትሮ የይዘት እና ስትራቴጂ ግንኙነት ጽ/ቤት አማካይነት የህዝብ ግንኙነት እና ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ እና ለማካሄድ ቀጣይነትን እና ጥራትን ማረጋገጥ።
- ገንዘብን በተመለከተ ኃላፊነት ያለው እና ተግባራዊ የህዝብ ግንኙነትን እና ተደራሽነት ማከናወን።
- የህዝብ ተሳትፎ ውጤቶችን ለሁሉም ለሚመለከታቸው ሠራተኞች እና ለሜትሮ የቦርድ ዲሬክተሮች ማሳወቅ።
- የህዝብ ተደራሽነት ውጤቶችን ውጤታማነት በሜትሮ በተቋቋሙ የአፈፃፀም መለኪያዎች መገምገም እና የማስተካከያ እርምጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ ተግባራዊ ማድረግ።

ከህዝብ ተሳትፎ የመጀመሪያ ዕቅድ ሂደት ቁልፍ ግኝቶች

በየመጀመሪያው የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ሂደት ውስጥ የነበሩ ቁልፍ ግኝቶች አሁንም ለዚህ እትም እውነት ናቸው። እነዚህ ግኝቶች የግንኙነት እና ተደራሽነት ዕቅዶችን ለመቅረፅ እና ለብዙ ስኬቶች ጠንካራ መሠረት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል። ሜትሮ አሁንም መከተል ያለበት የታረሙት ቁልፍ ግኝቶች ከዚህ በታች ይገኛሉ።

- የአንቀጽ 6 ህዝቦችን ለማሳተፍ ወደሚገኙበት ሥፍራ መሄድ። አናሳዎች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ እና ምንም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ለሌላቸው ዝግጅቶች በማዘጋጀት ወይም መረጃ በሚገኙበት ሥፍራ - እንደ መጓጓዣ ማዕከላት፣ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጭዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ ስልጠናዎች፣ የታቀዱ ህትመቶች እና ክብረ በዓላት - ለመድረስ በጣም ውጤታማው ዘዴ ነው።

- ባህላዊ ስሜታዊነትን ማሳየት። ተገቢውን የሜትሮ ሠራተኛ (ርዕሰ ጉዳይ፣ ባህላዊ እና የቋንቋ ብቃት) ወደ ዝግጅቶች እና ስብሰባዎች በማምጣት እና በቁሳቁሶች ውስጥ ተገቢ ውክልና በማሳየት ታዳሚዎችዎን ይወቁ።

- አስተያየቶቻቸውን ማግኘት ከሚፈልጉት ቡድኖች ፍላጎት ጋር ለማጣጣም፣ ዝግጅቶችን ለመካፈል አመቺ እና የዝግጅት ቅርፀቶች ከተሳታፊዎች ምርጫዎች ጋር እንዲጣጣም አመቺ ማድረግ። የስብሰባ ቅርፀቶች ከግለሰቦች ወይም ከማህበረሰቦች ምርጫዎች ጋር መመጣጠን አለባቸው - ይህ በአካል እና ምናባዊን ያካትታል። ወላጆችም በስብሰባው ላይ እንዲገኙ እና እንዲሳተፉ ልጆችን ያካተቱ እንቅስቃሴዎች ለማካተት ከግምት ውስጥ ማስገባት።

- ሰነዶችን ይተርጉሙ እና በዓለም ዙሪያ እውቅና ያላቸውን ግራፊክስ ይጠቀሙ። የመረጃ ሰነዶች አድማጮች በሚመርጡት ቋንቋ መሆን አለባቸው እና ታዳሚዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በባህላዊ አግባብ የተቀየሱ እና ቴክስት እና ግራፊክስ በመጠቀም ግልጽ መልዕክት ማስተላለፍ አለባቸው።

- ሚዲያዎችን በተለያዩ ቋንቋዎች ይጠቀሙ እና የተለያዩ ማሰራጫ መንገዶችን ይጠቀሙ። ሰነዶች በተለያዩ ቦታዎች እና ተሳፋሪዎች በሚያዘወትሩባቸው ቦታዎች፣ በአውቶቡስ ውስጥ፣ አውቶቡስ ማቆሚያዎች እና ሜትሮ ባቡር ጣቢያዎችን ጨምሮ መሰራጨት አለባቸው። በተጨማሪም፣ ሰነዶች ከመጓጓዣ ጋር የማይገናኙ እንደ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ በቤተ መጻህፍት፣ በምግብ መደብሮች እና በመኖሪያ ቤቶች መሰራጨት አለባቸው። የጋዜጣ ማስታወቂያ አሁንም ይሠራል እና ለብዙ ሰዎች የማህበረሰብ መረጃን ለመቀበል ተመራጭ መንገድ ነው።

- ለግብዓት ዕውቅና መስጠት እና መጠቀም። በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የህዝብ አስተያየት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ግልጽ መሆን አለበት።

- ዋና መምሪያን ያካተተ ለህዝብ ተሳትፎ ድርጅታዊ መዋቅር መመስረት። የህዝብ ተሳትፎ እና/ወይም የብዙ ዲፓርተመንቶችን ተሳትፎ ሂደትን የሚቆጣጠር ዲፓርትመንት በሥራ ላይ መዋል አለበት።

- ከተለያዩ ህዝቦች ጋር ግንኙነቶችን እና መተማመንን ለመገንባት ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ይሥሩ። እነዚህ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ቡድኖች አካባቢያዊ ማህበረሰቦችን ስለሚደግፉ ለትራንሲት ኤጀንሲ በየግዜው እምነትን ለማዳበር እና የጋራ ጠቃሚ ግንኙነቶችን ለማዳበር የሚያስፈልገውን ተደጋጋሚ ግንኙነት ለማመቻቸት በጣም ውጤታማ ምንጮች ናቸው።

- መረጃውን ለማዳረስ የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀሙ። መረጃዎችን በተወሰኑ አካባቢዎች ለቤተሰቦች ለማዳረስ ወይም ከቤት-ወደ-ቤት ለማሰራጭት ሌሎች ቴክኒኮችን እንደ የተማሪ ሪፓርት ካርድ ማሰራጫ ጊዜዎችን መጠቀም።

- ቴክኖሎጂን በአግባቡ ይጠቀሙ። በህዝብ ተሳትፎ ውስጥ የራሱ ቦታ ቢኖረውም፣ ቴክኖሎጂ ሌሎች የተደራሽነት መንገዶችን መጨመር አለበት። ምንም እንኳን ለኮቪድ -19 ወረርሽኝ የቴክኖሎጂ ጥቅም የበለጠ አስፈላጊ ቢሆንም ሁሉንም ያካተተ ለመሆን አድማጮቹን እና የመጠቀም ፍላጎታችወን ከግምት ውስጥ ማስገባትን አለበት።

- የሚያሳስቧቸውን ጉዳዮች በሚመለከት የሕብረተሰቡ ዓባላት ለሜትሮ ግብረመልስ እንዲሰጡ ለማስቻል ተደጋጋሚ የሕዝብ መድረክን ይጠቀሙ። ይህ ግብረመልስ በተወሰኑ ፕሮጀክቶች፣ ሀሳቦች እና ዕቅዶች ላይ አስተያየት ለመስጠት ነባር ዕድሎችን ያሚላል።

የፌደራል እና ሜትሮ ኮምፓክት (Compact) መስፈርቶች

የ FTA 4702.1B ሰርኩላር “ለፌዴራል ትራንስፖርት አስተዳደር ተቀባዮች የአንቀጽ 6 መስፈርቶች እና መመሪያዎች” ለፌደራል አንቀጽ 6 ተገዥነት እና መመሪያዎች ዋና ምንጭ ነው፤ ሆኖም ሙሉ፣ ፍትሃዊ እና ትርጉም ያለው የህዝብ ግንኙነት እና ተደራሽነትን በተመለከተ መመሪያ የሚሰጠው ብቸኛው የፌዴራል ደንብ አይደለም።

ሜትሮ የ FTA የከተማ አካባቢ ጠመር ድጋፎች ተቀባይ እንደመሆኑ፣ የህዝብ መደመጦች ዕድሎችን እና መረጃዎችን ለህዝብ ማድረስ አለበት። በተጨማሪም፣ FTA እና የዩ.ኤስ. የትራንስፖርት መምሪያ (USDOT) አነስተኛ እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ህዝቦች ላይ ያልተመጣጠነ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመከላከል የትራንስፖርት ኤጀንሲዎች በዕቅዳቸው፣ በፕሮጀክቶቻቸው እና እንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ አካባቢያዊ የፍትህ መርሆዎችን እንዲያካትቱ መምሪያ ይሰጣሉ። USDOT እንደ ሌሎች የፌዴራል ኤጀንሲዎች በብሔራዊ የአካባቢ ፖሊሲ ድንጋጌ (NEPA) መሠረት በአካባቢ ግምገማ ሂደቶች ውስጥ የህዝቡን ተሳትፎ ይጠይቃል።

የሜትሮ ኮምፓክት (Compact) በተጨማሪ ስለ ህዝብ መደመጥ አስፈላጊ ነገሮች እና መምሪያዎችን ጨምሮ በህዝብ ተሳትፎ መስፈርቶች ላይ መመሪያም ሰጥቷል። ስለ ፌዴራል እና ሜትሮ ኮምፓክት (Compact) መስፈርቶች ተጨማሪ ዝርዝሮች በአባሪ ሀ-የፌዴራል እና የሜትሮ ኮምፓክት (Compact) መስፈርቶች ግምገማ ውስጥ ማየት ይቻላል።

የወቅቱ የአመራር ተነሳሳሽነቶች

የሜትሮ የቦርድ ድሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስኪያጅ/ዋና ሥራ አመራር እና ሥራ አስፈፃሚ ቡድን ሜትሮን በብሔራዊ ዋና ከተማ ክልል ውስጥ ተመራጭ የትራንስፖርት አቅራቢ እና ቀጣሪ ለማድረግ ያተኮሩ ናቸው። በቅርብ ዓመታት ውስጥ በሜትሮ አሠራር ሥርዓት ደህንነት ላይ ህዝባዊ አመኔታን የሚያድሱ፣ የባቡር እና የአውቶቡስ መስመሮች ሰዓታቸውን በተሻለ ሁኔታ ጠብቀው እንዲሠሩ፣ እና የህዝቡ ገንዘብ በብቃት መተዳደርን ለማረጋገጥ የሥልጣንን ፋይናንስ በብቃት ሥልጣኑን ፋይናንስ በብቃት ማስተዳደር ፕሮጀክቶች ላይ ሠርተዋል፡፡ በእነዚህ ጥረቶች ከኮቪድ -19 በፊት የተሳፋሪዎች ቁጥር በመጨመሩ በሥራዓቱ ደህንነት እና አስተማማኝነት ላይ ለህዝቡ የታደሰ እምነት አስከትለዋል።

በ 2020 መጀመሪያ ላይ የተሳፋሪዎች ቁጥር መጨመር፣ የ Covid -19 ወረርሽኝ አካባቢውን ቀጥ አድርጎ ሲያስቆመው ሜትሮ የሠራተኞቹን እና ደንበኞቹን ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የጉዞ አገልግሎትን በመቀጠል በአጠቃላይ የአውቶቡስ እና ባቡር አገልግሎትን በመቀነስ ምላሽ ሰጠ። የሜትሮ ከወረርሽኝ መልሶ የማገገሚያ ዕቅድም የሠራተኞችን እና የደንበኞችን ደህንነት በመጠበቅ፣ የክልሉን የጉዞ ፍላጎቶች ለሟሟላት የተቀየሰ ነው፣ እንዲሁም ሜትሮ ለድህረ-ወረርሽኝ ክንዋኔዎች ጠንካራ እና መቋቋም የሚችሉ እርምጃዎችን ለመንደፍ የተቀየሰ ነው።

በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ ሜትሮ በ 10 ዓመት የ 15 ቢሊዮን ዶላር ካፒታል መርሃግብሩ አማካይነት በሥርዓት፣ በደህንነት፣ በአስተማማኝነት እና በክልሉ ኢኮኖሚ ውስጥ ኢንቨስት ማድረጉን ቀጥሏል። በሜትሮ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሜሪላንድ፣ ከቨርጂኒያ እና ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የካፒታል መርሃግብሩ ተጠናክሯል። በሚቀጥሉት ዓመታት ፕሮጀክቶች እየተጠናከሩ ሲሄዱ ሜትሮ የግንባታ እና የእድሳት ፕሮጀክቶች በጉዟቸው ላይ ሊኖራቸው ስለሚችለው ተጽዕኖ እና እነኝህ ፕሮጀክቶች ለክልሉ የሚያመጡትን ጥቅማጥቅሞችን ማሳውቅ ላይ ትኩረት ይሰጣል።

የሜትሮ የቦርድ ድይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የሜትሮ አመራር ዓባላት ለትራንስፖርት ፍትሃዊነት ያላቸውን ቁርጠኝነት፣ በሜትሮ ጅምሮች ስኬት ላይ የማህረሰቡ አስተዋጽዖ ያለው ወሳኝ ሚና እና በፕሮጀክት ማስተዋወቅ ውስጥ ግልፅነት አስፈላጊ ስለመሆኑ በሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የሜትሮ ዋና ሥራ አስኪያጅ/ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና የሥራ አስተዳደር ቡድን ሜትሮን በብሔራዊ ከተማ ክልል ምርጥ የትራንስፖርት አቅራቢ እና ቀጣሪ ለማድረግ ያተኮሩ ናቸው።

በሜትሮ አገልግሎት ክልል ውስጥ በአንቀጽ 6 የተካተቱትን ህዝቦች ሁኔታ እና መጠን መገንዘብ ለባህላዊ ስሜት፣ ለግንኙነቶች እና ተደራሽነት የተሻለ አቀራረብ ይሰጣል።

ሜትሮ በ 1,500 ካሬ ማይል የአገልግሎት ክልል ውስጥ አራት ሚሊዮን ነዋሪዎችን ያገለግላል። የትራንስፖርት ክልሉ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ የሜሪላንድ አውራጃዎችን፣ ሞንትጎመሪ እና ፕሪንስ ጆርጅን፣ የሰሜን ቨርጂኒያ አውራጃዎችን፣ አርሊንግተን፣ ፌርፋክስ እና ሎውደን እና የአሌክሳንድሪያ፣ የፌርፋክስ እና ፎልስ ቸርችን ያካትታል። በአጠቃላይ ፣ በመሃል ከተማ ውስጥ ከሚሠሩት መካከል - 45% - ዋሽንግተን እና አርሊንግተን ካውንቲ በከፊል - የህዝብ መጓጓዣ ይጠቀማሉ። የዚህ የአገልግሎት አካባቢ የስነ-ህዝብ ገጽታ 60% አናሳ ሲሆን በአገልግሎት መስጫ ስፍራው ከሚገኙት ቤተሰቦች ውስጥ 9% የሚሆኑት በድህነት ወለል ወይም በታች ናቸው (ከዚህ በታች ይመልከቱ)።



የአገልግሎት ክልል ስነ-ህዝብ ስብጥር

በየሜትሮ አገልግሎት አካባቢ ከሚኖሩ የተለያዩ አናሳ ቋንቋ ተናጋሪ ተወላጆች ውስጥ ብዙ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ይካተታሉ። በአሜሪካ የ 2015 የሕዝብ ቆጠራ የአሜሪካ ማህበረሰብ ጥናት የአምስት ዓመት ግምት መሠረት በአከባቢው ከሚኖሩት - ዕድሜያቸው - አምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ - 11.5% ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ (LEP) ያላቸው ናቸው።

በአገልግሎት አካባቢ ከሚገኙት አጠቃላይ LEP ቤተሰቦች ውስጥ 60% የስፓኒሽ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው። ሌሎች ከፍተኛ ቋንቋዎች ማንዳሪን፣ የቻይንኛ ማንደሪንኛ፣ ኮሪያንኛ፣ ቬትናሚኛ፣ የአፍሪካ ቋንቋዎች፣ ፈረንሳይኛ፣ ታጋሎግ እና አረብኛ ይገኙበታል።

333



ሜትሮ በባቡር ጣቢያዎች እና ተሳፋሪ ባለባቸው አውቶቡሶች የዳሰሳ ጥናቶችን በማካሄድ የአውቶቡስ እና የባቡር ተሳፋሪዎችን ስብጥር እና ስነ-ህዝብ አዘውትሮ ይለካል። በደንበኞች ምርምር ጽሕፈት ቤት የሚመራው ይህ የተሳፋሪዎች ጥናት መርሃ ግብር የፌዴራል የጊዜ ሰሌዳን ይከተላል።

በዚህ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ሜትሮ አናሳ እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የስነ-ህዝብ ገጽታዎችን በሥርዓት እና በትራንስፖርት ዓይነት (ሜትሮባቡር እና ሜትሮአውቶቡስ) አደራጅቷል። ዝቅተኛ ገቢ ከ 30,000 ዶላር በታች የሆነ የቤተሰብ ገቢ ተደርጎ ተወስኗል። በተጨማሪም፣ ሜትሮ በተወሰነ ርቀት ውስጥ ባለው የ LEP ቤተሰቦች መረጃ መሠረት ለእነዚህ ጣቢያዎች እና መስመሮች የቋንቋ መገለጫዎችን አዘጋጅቷል። ስለ እነዚህ ስነ-ህዝብ መግለጫዎች የበለጠ ዝርዝር መረጃ በአባሪ ለ: የስነ-ህዝብ ገጽታ መረጃ ይገኛል።

የሜትሮ-ደንበኛ ስነህዝብ ገጽታ፣ ሁሉም ሞዶች



የስነ-ህዝብ ቡድን

አናሳ	ባቡር	አውቶቡስ
ጥቁር/አፍሪካን-አሜሪካን	26%	58%
ስፓኝ	8%	16%
እስያዊ/ፓስፊክ አይላንደር	7%	6%
ዝቅተኛ-ገቢ	13%	46%
ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ	5%	27%

የሜትሮ ስትራተጃዊ ዓላማዎች በሥራ ላይ ያሉ እና የረጅም-ጊዜ ፕሮግራሞችን የሚቆጣጠረው ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾችን (KPI) ጨምሮ በሁሉም ደረጃዎች በአጠቃላይ በአመራሩ የአሠራር ቁጥጥርና ግምገማ ቁርጠኛ ነው። ሜትሮ ለአሠራር ቁጥጥር ያለውን ቁርጠኝነት ለማንፀባረቅ እና በየሦስት ዓመቱ የአንቀጽ 6 ፕሮግራሙን ለማሻሻል የሚያስፈልገውን መስፈርት ለማሟላት ለአጠቃላይ ዕቅድ እንዲሁም ለግለሰብ ፕሮጀክት ጥረቶች የአፈፃፀም መለኪያ ማዕቀፍ አዘጋጅቷል።

ሜትሮ እነዚህን የአፈፃፀም መለኪያዎች ከሁሉም ፕሮጀክቶች "ከተገኙት ትምህርቶች" ጋር ለመገምገም በአመራሩ የተዘጋጀውን ጠንካራ የኦንላይን መከታተያ፣ የህዝብ ተሳትፎ አስተዳደር ስርዓት (PPMS) የተባለውን መሣሪያ ይጠቀማል። ሠራተኞቹ እነዚህን ውጤቶች በመገምገም በወቅታዊ የአሠራር ዘዴዎችና ሂደቶች ላይ የተገኙ ስኬቶችና ማሻሻያዎች ላይ ለመወያየት ከውስጥ እና ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለማቋረጥ ይገናኛሉ።

42 METRO CENTER

ለህዝብ ግንኙነት እና ለታቀዱ ፕሮጀክቶች ተደራሽነት መመሪያዎች

በደንበኞች ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ የፕሮጀክቶች ብዛት እና መጠን፣ በተለይ እየጨመረ በሚሄደው የሜትሮ ካፒታል ፕሮግራም የተነሳ ሜትሮ ፈጣን የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች እያየ ነው። በይዘት እና ስትራተጂ ኮሚዩኒኬሽን (CASC) የሚተዳደረው የሜትሮ ደረጃውን የጠበቀ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ሂደት፣ የፌዴራል ትራንስፖርት አስተዳደር (FTA) ደንቦች መከበራቸውን እና ግንኙነቶች፣ የታቀዱ ፕሮጀክቶች እና የፖሊሲ ውጥኖች ሁሉን ያካተቱ፣ ተባባሪ እና ለማህበረሰቡ ፍላጎቶች ምላሽ ሰጭ መሆናቸውን ያረጋግጣል። በዕቅዱ ውስጥ የተቀመጡት ስልቶች የተለያዩ የሜትሮ ደንበኞች፣ አናሳ ህዝቦች እና ውስን እና ምንም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ የሌላቸው ህዝቦች ተሳታፊ መሆናቸውን እና መረጃ ማግኘታቸውን ያረጋግጣሉ።

አንዴ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ እና የደንበኛ ወይም የማህበረሰብ ተጽዕኖዎች እንዳሉት ከተወሰነ - በሜትሮ ውስጥ ቢመሩ ወይም ፕሮጀክቶቻቸው በሜትሮ ደንበኞቻቸው ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ የውጭ ድርጅቶች ወይም ተቋራጮች የሚመሩ ከሆነ - የፕሮጀክቱ ዕቅድ ሁሉንም የሚያካትት እና ቀልጣፋ የሆኑ የግንኙነት እና ተደራሽነት ስልቶችን የሚደግፉ አካላትን ለማካተት የተዘጋጀ መሆን አለበት። የሚቀጥለው ምዕራፍ ሜትሮ እና አዋሳኝ ፕሮጀክቶች በደንበኞች ወይም በአከባቢው ማህበረሰብ ላይ ተጽዕኖ በሚያስከትሉበት ጊዜ መከተል ያለባቸውን ሂደት እና መመሪያዎች እይታ ይሰጣል።

የፕሮጀክቱ ጀማሬ

የግንኙነት ዕቅድ ሂደት

የግንኙነት ዕቅድ አፈጻጸም

ቁጥጥር፣ ክትትል እና ሪፖርት ማድረግ

በሜትሮ ውስጥም ሆነ ከውጭ ባለ የሜትሮ ንብረት አጠገብ የሆነ አንድ ፕሮጀክት ሲጀመር፣ የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ እና የፕሮጀክቱ መጨረሻው ውጤት እስከሚፈጸም በደንበኞች እና የማህበረሰብ ዓባላት ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ ፕሮጀክቱ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድን ይቀሰቅስ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ የመለየት፣ የፕሮጀክቱን ስፋት እና ተጽዕኖን መገምገም እና የምዝገባ ሂደቱን ለመጀመር የሜትሮ የይዘት እና ስትራቴጂ ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት (CASC) ጋር የመገናኘት ተልዕኮ ተሰጥቶታል።

መስመርቱን የሚያሟሉ ፕሮጀክቶች

ሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዱን (PPP) ተገዢነት የሚያነሳሱ የተለያዩ ፕሮጀክቶች እና ዕቅዶች አሉት። በአጠቃላይ ማንኛውም የታቀደ ፕሮጀክት - ወይም ድንገተኛ-ያልሆነ ፕሮጀክት - የሜትሮ ደንበኛ ወይም የአካባቢ ማህበረሰብ ተጽዕኖ ያለው ወይም እንደ ሜትሮ ኮምፓክት (Compact) ወይም FTA ካሉ ሌሎች መመሪያዎች የህዝብ አስተያየትን የሚፈልግ ፕሮጀክት የ PPP መመሪያዎችን መከተል አለበት። የ PPPን ተገዢነት የሚቀሰቅሱ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን፣ ግን በነሱ ብቻ ሳይወሰኑ፣ ያካትታሉ፤

ጥናቶች እና ሙከራዎች

ምሳሌዎች የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የሙከራ መርሃ ግብሮች፣ የጣቢያ አካባቢ ዕቅድ ፕሮጀክቶች፣ ወይም የአውቶቡስ፣ የባቡር፣ የመኪና ማቆሚያ ወይም የዋጋ ጥናቶችን ጨምሮ የረጅም እና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ጥናቶችን ያካትታሉ።

አገልግሎቶች፣ የአካባቢ እና የመሠረተ ልማት ለውጦች

ምሳሌዎች የደንበኞችን ባህሪ ወይም የጉዞ መዳረሻ፣ የመክፈቻ፣ የደንበኛ መገልገያዎችን መክፈት፣ መቀየር እና መዝጋት፣ የመገናኛ ብዙሃን ወይም የግዢ ለውጦችን ያካተቱ አዳዲስ ስርዓቶችን እና መዋቅሮችን ያጠቃልላሉ። ይህ የ NEPA የአካባቢ ግምገማዎችን እና የተፅእኖ ሪፖርቶች የሚጠይቁ እና/ወይም የጅምላ መተላለፊያ እቅድን የሚያሻሽል ማንኛውንም ፕሮጀክቶች ያካትታል።

የአገልግሎት ለውጦች

ምሳሌዎች መስመሮችን መለወጥ፣ የሰዓታት መጠን ወይም የአገልግሎት ድግግሞሽ፣ በተለይም የእኩልነት መብት ትንተና እና/ወይም የኮምፓክት ችሎት የሚያስፈልጋቸው እንደ ዋና የአገልግሎት ለውጦችን ያካትታሉ፡፡

የፖሊሲ አማራጮች እና የዋጋ ለውጦች

ምሳሌዎች የፖሊሲ ተነሳሳሽነቶችን ወይም የደንበኞች ተጽዕኖዎች እና የዋጋ ለውጦችን ያካትታሉ፡፡

የህዝብ መረጃ እና ማስታወቂያ

ምሳሌዎች የሜትሮ ደንበኞች ወይም በሜትሮ ሥልጣን ሥር የሚገኙ ማህበረሰቦችን እንደ በሜትሮ ተቋም ውስጥ ያሉ ግንባታዎችን፣ የታቀዱ ለረጅም ጊዜ የተዘጉ መተላለፊያዎችን፣ የመልሶ ማቋቋም እና የመልሶ ግንባታ ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም በሜትሮ ደንበኞች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የጋራ ውጥኖች/በአጠገብ ያሉ የግንባታ/የሥልጣን ፕሮጀክቶችን በመሳሰሉ የሜትሮ ደንበኞችን ወይም የሥልጣን ማህበረሰቦች ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ አስፈላጊ ወይም የታቀዱ ሥራዎችን ያጠቃልላሉ።

በ “WMATA ኮምፓክት (Compac) ስር የህዝብ ችሎት የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ከኮምፓክት (Compact) ደረጃዎች ጋር ከመጣጣም በተጨማሪ ከ PPP ጋር መጣጣምን ያነሳሳሉ።

ለድንገተኛ ጊዜ ጥገናዎች ወይም በደንበኞች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ፕሮጀክቶች፣ ሜትሮ በተቻለ መጠን የ PPP የግንኙነት ፕሮቶኮልን ለመከታተል ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

በፕሮጀክቱ ወሰን ውስጥ የማህበረሰብ እና የደንበኞች ተሳትፎ ዕድሎችን እና ተጽዕኖዎችን መገንዘብ

የፕሮጀክቱ ሂደት ጅመራ ለፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች እና ባለቤቶች ስለ ደንበኛ ወይም ስለ ማህበረሰብ ተጽዕኖዎች ማሰብ መጀመር እና እነኝህ ቡድኖች ፕሮጀክቱ በሚካሄድበት ጊዜ አስተያየት እንዲሰጡ እንዴት ማሳተፍ እንደሚቻል ማሰብ የሚጀምሩበት ወሳኝ ጊዜ ነው። በተጨማሪም፣ CASC ን በግንኙነት እና ተደራሽነት ምሥረታ ላይ ለማሳተፍ ይህ የተሻለ ጊዜ ነው። የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች እና ባለቤቶች ግንዛቤ ውስጥ ማሰገባት ያለባቸው ጥቂት ምሳሌዎች፣

- የፕሮጀክቱ የሥራ መጠን የአሠራር ለውጦችን የሚፈልግ ከሆነ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤቱ ፈቃድ ያለው የሥራ ዕቅድ ወይም የትራንስፖርት ጥገና (MOT) ዕቅድ ለማዘጋጀት ከውስጥ ባለድርሻዎች እና ከተገቢ የሥልጣን አጋሮች ጋር መሥራት አለባቸው። ይህ ከ CASC ምዝገባ ሂደት በፊት መሆን አለበት።
- የፕሮጀክቱ ሂደት ገና በዝግጅት ላይ ከሆነ ወይም ተጽዕኖ ካደረሰ ወይም የተሳትፎ ስልቶች በዚህ ደረጃ ሊታወቁ የማይችሉ ከሆነ፣ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤቱ ከ CASC ጋር የምዝገባ ሂደቱን መጀመር አለባቸው። ሆኖም፣ መረጃው መቼ በሥራ ላይ እንደሚውል የጊዜ ገድብ ማዘጋጀት አለባቸው።
- ፕሮጀክቱ፣ የሥራ ወሰን፣ የተግባር ቅደም ተከተል፣ ስምምነት ወይም ኮንትራት በማዘጋጀት ላይ ከሆነ እና የደንበኛ ወይም የማህበረሰብ ተጽዕኖዎች እና ተሳትፎ መካተት ያለበት ከሆነ፣ የፕሮጀክቱ ቡድን ይዘትን ለማቅረብ፣ የግምገማ መመዘኛዎችን ለመጻፍ ወይም የረቂቁን ወሰኖችን መገምገም እንዲችሉ ከ CASC ጋር የሚደረገው የምዝገባ ሂደት ባስችኳይ መጀመር አለበት።
- ፕሮጀክቱ የደንበኞች ተጽዕኖዎች ሊኖረው የሚችል ከሆነ ግን ባሁኑ ሂደቱ የግንኙነት ወይም ተደራሽነት ኮንትራት ከሌለው የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤቱ ይህንን ተግባር ለማካተት ሂደቱን መለወጥ ወይም ሥራው በውስጥ ምንጭ ሊጠናቀቅ እንደሚችል ከ CASC ፈቃድ ማግኘት ያስፈልገው ይሆናል።

ከሜትሮ ስትራቴጂ ዓላማዎች ጋር ለማጣጣም እና የፕሮጀክቱን ሂደቶች ለማረጋገጥ ቁልፍ የሆኑ የውስጥ ባለድርሻ አካላት ከፕሮጀክቱ ጅምር መካተት አለባቸው። ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት መካከል ብዙዎቹ ፕሮጀክቱ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል መተንበይ ወይም መለየት ይችላሉ - በተለይም በኦፕሬሽን እቅድ ዙሪያ - የትኞቹ ጉዳዮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ እና የደንበኞችን፣ የህብረተሰቡን እና የተሳፋሪዎች ተፅእኖን ለመቀነስ ምን ዓይነት ለውጦች ሊተገበሩ እንደሚችሉን ጨምሮ ያካትታል።

ፕሮጀክቱ ሲጀመር ተገቢውን የባለድርሻ አካላት ለይቶ ማወቅ እና ማካተት የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም የሥራ አስኪያጁ ኃላፊነት ነው። የባለድርሻ አካላት ከታወቁ በኋላ በፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ የተዘጋጀ የጅምር ስብሰባ የዚህ የመጀመሪያ ሂደት አካል እንዲሆን በጥብቅ ይመከራል፣ እናም ውይይቱ የህብረተሰቡን እና የደንበኞችን ተጽዕኖ የሚጠቁሙ ውይይቶችን ማካተት አለበት።

የውስጥ ሜትሮ ባለድርሻ አካላት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ ግን አይገደቡም፣

ዋና አማካሪ፣ ሜትሮ ኮምፓክት (Compact)፣ FTA ወይም NEPA ተገዢነት፣ ወዘተ።

የሜትሮ ትራንዚት ፖሊስ መምሪያ/የአስቸኳይ ጊዜ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ የመግቢያ ተጽዕኖዎች፣ የጣቢያ ውቅር፣ ወዘተ።

የ አካል ጉዳተኞች (ADA) ፖሊሲ እና ዕቅድ ቢሮ፣ የ ADA ተገዢነት፣ የእግረኞች ተደራሽነት ተጽዕኖዎች፣ የመግቢያ/መወጣጫ/ኤሊቬተር ተጽዕኖዎች፣ የ ADA የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን መዘጋት፣ ወዘተ።

የቦርዱ ፀኃፊ ጽ/ቤት፣ የቦርዱ ግንኙነት እና ማፅደቆች፣ ወዘተ።

የአውቶብስ ዕቅድ ቢሮ፣ የመንገድ መዘጋት ተጽዕኖዎች፣ የአውቶቡስ ማቆሚያ፣ የሉፕ ወይም የትራንዚት ማዕከል ተጽዕኖዎች፣ ወዘተ።

የመንገድ ጥገና መሃንዲስ ዋና ጽ/ቤት፣ የእግር መንገድ መብቶች እና ተደራሽነት፣ ወዘተ።

የደንበኞች ጥናት ቢሮ፣ የተጠቃሚ ጥናት፣ የሙከራ ግብረመልስ፣ ወዘተ።

እኩል የሥራ መብት ቢሮ፣ የፍትሃዊነት ጉዳዮች፣ ግምገማዎች እና የቋንቋ ድጋፍ ዕቅድ መስፈርቶች

የኤልቬተር እና መወጣጫዎች ጽ/ቤት፣ የመግቢያ/መወጣጫ/ኤሊቬተር ተጽዕኖዎች፣ የጣቢያ ውቅር፣ ወዘተ።

የመንግሥት ግንኙነት ጽ/ቤት፡ የማህበረሰብ አከባቢ ተጽዕኖዎች፣ የተመረጠ ባለሥልጣን ወይም የስሥጣን ባለድርሻ አካላት መታወቂያ፣ ወዘተ።

የፋብሪካ ጥገና ቢሮ፣ የመግቢያ ተጽዕኖዎች ፣ የጣቢያ ውቅር ፣ የጣቢያ ሀብቶች ጥገና ፣ ወዘተ፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት እና የመኪና ማቆሚያ ቢሮ፣ ፈቃዶች፣ የንብረት መስመሮች፣ የመንገድ መዘጋት ተጽዕኖዎች፣ የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ ወይም የመስነባበቻ ቦታ ተጽዕኖዎች፣ የብስክሌት እና የመሳፈር ተጽዕኖዎች፣ ወዘተ።

የባቡር ትራንስፖርት ጽ/ቤት፣ መግቢያ/መወጣጫ/ኤልቨተር ተጽዕኖ፣ የጣቢያ ውቅር፣ ወዘተ።

የፕሮጀክት ስብሰባዎች ከጅምሩ ሁሉን አቀፍ እና መረጃ ሰጭ እንዲሆኑ CASC በተጨማሪም በተገቢው የውስጥ ባለድርሻ አካላት ላይ የፕሮጀክት ባለቤቶች እና ሥራ አስኪያጆችን ለመምከር ይገኛል።

የምዝገባ ሂደት፣ የይዘት እና ስትራቴጂ ግንኙነቶች ጽ/ቤት

አንዴ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድን ተገዢ የሚያደርግ ፕሮጀክት እንደ ብቁ ፕሮጀክት ሆኖ ከተጠቆመ እና የደንበኛ ወይም የህብረተሰብ ተጽዕኖ ወይም በፕሮጀክቱ ሂደት ተሳትፎ የሚከሰት ከሆነ፣ የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ የፕሮጀክቱ ይዞታ እና ስትራተጂ ግንኙነቶች ቢሮ (CASC) ቅርንጫፍ ከሆነው ከደንበኞች አገልግሎት፣ ግንኙነት እና ማርኬቲንግ መምሪያ ጋር የምዝገባውን ሂደት መጀመር ይችላል።

የምዝገባ ሂደቱን ለመጀመር የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ በ CASC ውስጥ የታቀዱ ፕሮጀክቶች የግንኙነት እና ተሳትፎ አስተዳዳሪን የማነጋገር ኃላፊነት አለባቸው። አስተዳዳሪው በግንኙነት ዕቅዱ ከፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ጋር የሚሠራ የስትራተጂ ግንኙነት አስተዳዳሪ ወይም ሌላ የ CASC ቡድን ዓባል ይመድባሉ። የግንኙነት ዕቅዱ ከማንኛውም አስፈላጊ መረጃዎች ጋር እንዲጀመር እና እንዲስተገብር ለማስቻል የምዝገባው ሂደት በፕሮጀክቱ የሕይወት ዑደት ውስጥ ቀደም ብሎ መጀመር አለበት። እንደ ፕሮጀክቱ ሂደት ይዘት፣ ውጤቶች ወይም የህብረተሰብ ተሳትፎን ከመታያቸው በፊት ከሁለት ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ ሊወስድ ይችላል።

የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ በፕሮጀክቶቻቸው ዙሪያ የግንኙነት ዕቅዱን ለማዘጋጀት ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በዕቅዱ ውስጥ ያሉት ሁሉም ተግባራት መጠናቀቃቸውን ለማረጋገጥ እና የመልዕክት እና የግንኙነት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶች ላይ መመሪያ ለመስጠት CASC እንደ የግንኙነት ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤቱ ለፕሮጀክቱ አጠቃላይ አመራር (ማለትም የቦርዱ የአሠራር ጉዳዮች፣ ማጽደቆች፣ ሪፖርቶች) ኃላፊነቱን ይቀጥላሉ፣ እንዲሁም ማንኛውንም የግንኙነት እና ተደራሽነት ማጣቀሻዎች ከመታተም/ለቦርድ ዳይሬክተሮች ወይም ሌሎች ባለድርሻዎች ከመቅረባቸው በፊት በ CASC ተገምግመው መጽደቃቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

እያንዳንዱ የግንኙነት ዕቅድ በፕሮጀክቱ ስፋት፣ የደንበኞች ተጽዕኖ ደረጃዎች፣ የጊዜ ሰሌዳ እና በበጀት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ የሚከተለው ሂደት CASC በሥራ ላይ የሚውል እና የመመሪያዎችን ተገዢነትን የሚያረጋግጥ ዕቅድ ለማዘጋጀት ያስችለዋል፡፡

እንደ ያካባቢ ግንባታ ያሉ ከውጭ የሚካሄዱ እና የሜትሮ ደንበኞች ላይ ተጽዕኖ ለሚያመጡ ፕሮጀክቶች፣ የፕሮጀክት ቡድኖች የግንኙነቶች ዕቅድ አዘጋጅተው CASC እንዲገመግመውና እንዲያጸድቀው ማቅረብ አለባቸው፡፡

የፕሮጀክት ጅማሬ

የግንኙነት ዕቅድ ሂደት

የግንኘነት ዕቅድ አፈጻጸም

ቁጥጥር፣ ክትትል እና ሪፖርት ማድረግ



ደረጃ አንድ: የፕሮጀክት መረጃ መሰብሰብ

እንደ በምዝገባው ሂድት ክፍል፣ የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ የሚከተለውን መረጃ የመስጠት ኃላፊነት እና ዝግጁ መሆን አለበት፡፡

የሥራ መጠን እና የጊዜ ገደብ	የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ ማንኛውንም ስለ ፕሮጀችቱ ያሉ ዝርዝሮች፣ ተጽዕኖዎች እና ማሻሻያዎችን ጨምሮ፣ እና የሥራውን መጠን የሚያሳዩ ውጤቶችን፣ ማስታወሻዎችን ወይም ሪፖርቶችን ማካፈል አለባቸው። በተጨማሪም፣ የስኬት ቀናት፣ የማስረከቢያ ቀነ-ገደቦች ወይም የቦርድ ማጽደቆች፣ የሥራ ጊዜ ገደብ ግምት፣ ወዘተ… መካተት አለባቸው። የቀረበው የጊዜ ገደብ ሁሉንም የፕሮጀክት ሥራዎች የሚያካትት ከሆነ የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ በደንበኛው ወይም በማህበረሰቡ ላይ ከሚደርሰው ተጽዕኖ ጋር የሚያያዘው የትኛው ሥራ እንደሆነ ማሳየት ወይም ግልጽ ማድረግ አለባቸው።
ተጽዕኖ የደረሰባቸው /የታቀዱ ታዳሚዎች እና ስነ-ህዝብ ስርጭት	የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ፣ በተቻለው መጠን ተጽዕኖ ሊደርስባቸው የሚችሉ እና/ወይም በፕሮጀክቱ ከፍተኛ ፍላጎት ወይም ድርሻ ያላቸውን ደንበኞች እና ህብረተሰብ መረጃ መስጠት አለበት። የስነ-ህዝብ መገለጫ መረጃ ተመራጭ ነው (አናሳ ማህበረሰቦች፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ ውስን ወይም ምንም እንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ የሌላቸው፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የዕድሜ ቡድኖች፣ ወዘተ) ግን ለፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ካልታወቁ CASC ይህንን መረጃ ለመሰብሰብ ከሌሎች ቢሮዎች ጋር ይሠራል።
በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ በጀት እና ሀብቶች	የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ ከግንኙነት እና ተደራሽነት ጥረቶች ጋር የተያያዙ የበጀት እና የንብረት መረጃዎች መስጠት አለባቸው። የወጪ መነሻ ወይም ንብረቶች ከጅምሩ ካልተገለጹ፣ CASC ለዕቅዱ ሂደት ሊገለገሉብት የሚያስችል የበጀት እና ንብረቶች ግምት ለፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ያዘጋጃል።
የደንበኞች እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች እና አስተዋጽዖ ዓላማ	የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ በተቻላቸው መጠን የግንኙነት ግቦች ናቸው ብለው የሚያምኑትን እና የሚመለከተው ከሆነ ምን ዓይነት ግብረመልስ ማግኘት እንደሚፈልጉ (ማለትም፣ ሠራተኞቹ ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚረዳቸው ምን ዓይነት ግብዓት ነው?) ማቅረብ አለባቸው። እነዚህን ግቦች መግለፅ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት አስፈላጊ ሲሆን CASC በመላው በፕሮጀክቱ ግንኙነት ዕቅድ ላይ የሚውል ትክክለኛውን መልዕክት እና መላዎች እንዲያዘጋጅ ይረዳዋል። ምሳሌዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ፣ ግን አይገደቡም፣ ይችላሉ: • **ትብብር፡** WMATA/የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ ፕሮጀክቱን በመተንተን፣ በአማራጮች እና/ወይም ከህዝብ ጋር በሚደረገው ውሳኔ ላይ ከህዝብ ጋር መተባበር ይፈልጋል። አማራጮችን ማዘጋጀት እና ተመራጭ መፍትሄዎችን መለየትን ሊያካትት ይችላል። • **ምክር፡ WMATA**/የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ በፕሮጀክቱ ሠራተኞች ወይም በቦርዱ በተዘጋጁ ትንተናዎች፣ አማራጮች እና/ወይም ውሳኔዎች ላይ አስተያየት ማግኘትን ጨምሮ በፕሮጀክቱ ላይ ከህብረተሰቡ ጋር መመካከር ካስፈለገው። • **መረጃ: -** WMATA/የፕሮጀክት ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ ፕሮጀክቱን በተመለከተ፣ ስለ ፖሊሲው ያጋጠሙ ችግሩ፣ አማራጮች፣ ዕድሎች እና/ወይም መፍትሄዎችን እና ከግምት ውስጥ የሚገቡ እውነታዎችን እና ዐውደ-ጽሑፎችን ጨምሮ ለህዝብ ማሳወቅ ይፈልጋሉ።
ቁልፍ ባለድርሻ አካላት	የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ ከተቻለ የባለድርሻ አካላት መዝገብ ወይም በማትሪክስ ቅርጸት የባለድርሻ አካላትን ዝርዝር ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ዝርዝሩ ከፕሮጀክቱ ጅምር አንስቶ ማንኛቸውም በደንበኛ ወይም በማህበረሰብ ተጽዕኖዎች ግንዛቤ ያላቸው እንዲሁም ከፍተኛ የጥቅም ፍላጎት ያላቸው እና/ወይም ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ቁልፍ ሰዎችን ማካተት አለበት። CASC ይህንን መረጃ ለማቅረብ የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ በመክፈቻ ስብሰባ ላይ እንዲሳተፉ ሊጠይቅ ይችላል። በፕሮጀክቱ ቡድን ውስጥ ይዘትን እና ቁሳቁሶችን ለማጋራት ምን ዓይነት የፕሮጀክት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (PMIS) ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ለመወሰን CASC ከፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ጋር አብሮ ይሠራል።

ደረጃ ሁለት፡ የግንኙነት ፕሮጀክት ቡድን ገለጻ

የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድን፣ የአንቀፅ 6 እና የአካል ጉዳተኞች (ADA) ደንቦችን፣ እና የ WMATA ኮምፓክት ተገዢነትን ለማረጋገጥ በሜትሮ ውስጥ ያሉ ብዙ ቁልፍ መምሪያዎች በመገናኛዎች ዕቅድ እና ትግበራ ሂደት ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

በፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ የቀረበውን የባለድርሻ አካላት ዝርዝር እንደ መነሻ በመጠቀም CASC ሌሎች ቢሮዎችን እና መምሪያዎችን የግንኙነቶች ፕሮጀክት ቡድኑን እንዲቀላቀሉ ሊጋብዝ ይችላል። በተለምዶ ንቁ ሚና ያላቸው የባልደረባ መምሪያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

- **የአካል ጉዳተኞች (ADA) ፖሊሲ እና ዕቅድ ቢሮ፣** የአካል ጉዳተኞች (ADA) ፖሊሲ እና ተገዢነት ኃላፊነት አለው። ለአካል ጉዳተኞች እና ለአዛውንቶች ተደራሽነት ፍላጎቶች ላይ ምክር ይሰጣል፣ ለተደራሽነት አማካሪ ኮሚቴ አገናኝ ሆኖ ያገለግላል፣ እንዲሁም በተደራሽነት ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ከክልል አውታረመረቦች ጋር ግንኙነቶችን ያስተዳድራል።

- **የቦርዱ ፀኃፊ ጽ/ቤት፣** ለሜትሮ ቦርድ ቁሳቁሶችን ማቀናበር፣ ግምገማ እና ስርጭት፣ ህዝባዊ ችሎቶች በማዘጋጀት ለ WMATA የቦርድ ድሬክተሮች ለተሳፋሪዎች አማካሪ ምክር ቤት እንደ አገናኝ ሆኖ ያገለግላል። ለሁሉም ፕሮጀክቶች የኮምፓክት መከበርን በተመለከተ ምክር ይሰጣል።

- **የደንበኞች ምርምር ጽ/ቤት፣** የደንበኞች ምርጫዎችን እና አስተያየቶችን ለመጠቆም፣ የጥራት እና የብዛት ጥናት ቁጥጥር ኃላፊነት ያለው እና በሜትሮ ፖሊሲ ውሳኔዎች ላይ ለደንበኛ አስተያየት ይሰጣል። የህዝብን አስተያየት እና የውጤቶችን ትንተና ለመሰብሰብ በላቁ ዘዴዎች ላይ ይመክራል፡፡

- **የእኩል የሥራ ስምሪት ዕድል ቢሮ፣** የአንቀጽ 6 እና የቋንቋ ድጋፍ ዕቅድ ፖሊሲን እና ተገዢነትን የመከታተል ኃላፊነት አለው። የቋንቋ ተደራሽነት እና የትርጉም/የማስተርጎም ፍላጎቶች ተገዢነትን በተመለከተ ምክር ይሰጣል እንዲሁም ከክልል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን ያስተዳድራል።

- **የመንግሥት ግንኙነት ጽ/ቤት፣** ለድጋፍ አገልግሎት ሃላፊነት ያለው እና ከፌዴራል፣ ስቴት እና ከአከባቢ ፖሊስ እና ከመንግሥት ተወካዮች ጋር እንደ አገናኝ ሆኖ ያገለግላል።

- **የዕቅድ ጽ/ቤት፣** ከአንቀጽ 6 ተገዢነት ጋር ለተያያዘው የቴክኒክ ትንተና፣ የአንቀጽ 6 የአገልግሎት እና የዋጋ ለውጦች ግምገማን ጨምሮ ኃላፊነት አለው። የስነ-ህዝብ እና የህዝብ ቆጠራ መረጃ አጠቃቀም ላይ ምክር ይሰጣል እንዲሁም የእኩልነት ትንተና ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት።

ሌሎች በደንበኞች አገልግሎት፣ ግንኙነት እና ማርኬቲንግ መምሪያ ውስጥ ያሉ መሥሪያ ቤቶችም እንደአስፈላጊነቱ ለመቀላቀል በ CASC ተለይተው ይጠቆማሉ። ተጨማሪ የቡድን ዓባላት በፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ንብረት ለማስተዳደር ሥራ (ግዥ፣ የሂሳብ መጠየቂያ ማቀነባበሪያ፣ ወዘተ) መጠቀም ይኖርባቸው ይሆናል።

የኃላፊነት ምደባ ማትሪክስ ወይም ዝርዝር የመጨረሻው የግንኙነት ዕቅድ አካል ይሆናል እና የእያንዳንዱን የቡድን ዓባል ሚና-ኃላፊነት-ሥልጣኖችን ያጠቃልላል።

ደረጃ ሶሥት፣ የግንኙነት መልዕክቶች እና ታክቲኮች

CASC ከግንኙነቶች ፕሮጀክት ቡድን ከሚያገኘው ግብዓት፣ ለግንኙነት ዕቅድ መልዕክት እና በጣም ተገቢ የሆኑ የግንኙት፣ ተደራሽነት እና የግብረመልስ ስልቶችን ይወስናሉ። እነዚህም በፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ በተሰጡ መረጃዎች፣ የፕሮጀክት መጠን እና ተጽዕኖዎቹ፣ የጊዜ ሰሌዳ፣ ተጽዕኖን /ዒላማ ያደረጉ ታዳሚዎች፣ የግንኙነት እና ግብረመልስ ግቦች እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ላይ የተመረኮዘ ይሆናል።

ስትራትጃዊ የመልዕክት መዋቅር ተዘጋጅቶ ለሁሉም የውስጥና የውጭ መልዕክቶች እንደ መመሪያ ሆኖ ያገለግላል። ይህም መዋቅር ከታቀዱት ታዳሚዎች የሚስማሙ፣ ግልጽ በሆነ መንገድና በዘላቂነት መልዕክቶች እንዲቀናበሩ እና በሁሉም ስልቶች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የተፈቀዱ ቁልፍ የመነጋገሪያ ነጥቦችን ለመቅረጽ ይረዳል። መልዕክቱ በተለያዩ የፕሮጀክቱ ደረጃዎች መገምገም እና መመዘን ሊያስፈልገው ይችል ይሆናል።

የግንኙነት ዕቅዱ የሜትሮ መመሪያ መርሆዎችን፣ ግቦችን፣ ዓላማዎችን እና ለህዝብ ተሳትፎ ቁልፍ ግኝቶችን ማንፀባረቅ አለበት (ምዕራፍ 1)። እያንዳንዱ ዕቅድ ውጤታማ የሆኑ የግንኙነት ጥረቶችን ለማረጋገጥ ተጽዕኖ ያደረባቸው ማህበረሰቦችን፣ በተለይ የአንቀጽ 6 ማህበረሰቦችን፣ ለመደረስ አስቸጋሪ ከሆነ፣ ምን ዓይነት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እና እልባቶች ጥቅም ላይ መዋል እንዳለባቸው ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

ሰዎችን ባሉበት ቦታ መድረስ

ተሳፋሪዎች ወይም ሌሎች የማህበረሰቡ ዓባላት ግብረመልስ ለመስጠት ወይም በእነሱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ፕሮጀክት ለማወቅ “ወደ እኛ ይመጣሉ” ብለው በጭራሽ አይጠብቁ። ተጽዕኖ የደረስባቸው ደንበኞች በሚገኙበት፣ በአውቶቡስ ማቆሚያ፣ በአካባቢ ድርጅቶች፣ በሜትሮባቡር ጣቢያ ወይም በማህበረሰብ ዝግጅቶች ላይ መገናኘት እና ግብረመልስ መሰብሰብ ያስፈልጋል።

ስለ ተሳትፎ ዕድሎች ለህብረተሰቡ ለማሳወቅ በርካታ አቀራረቦችን እና እንቅስቃሴዎችን ይጠቀሙ

ይህም የማህበረሰብ ድርጅቶችን እና ባለድርሻ አካላትን፣ ነጻ ሚድያ (የዜና ታሪኮች) ፣ የተለጠፉ ምልክቶችን ወይም የመኪና በራሪ ወረቀቶችን፣ ባለብዙ ቋንቋ ጋዜጦች ላይ በክፍያ የሚደረጉ ማስታወቂያዎች፣ በማህበራዊ ሚዲያዎች፣ በአካባቢ የሚካሄዱ ስብሰባዎች ላይ ዝግጅት ማቅረብን ሊያካትት ይችላል። እነዚህን ለማከናወን ዘይቤዎች በሚዳብሩበት ጊዜ ዝቅተኛ ትምህርት፣ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ እና የአካል እና የአእምሮ ጤና ጉዳተኛ ደንበኞችን ፍላጎቶች ሁሉ ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

ቴክኖሎጂን በአግባቡ ይጠቀሙ

የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እጅግ ጠቃሚ ሊሆን ስለሚችል በህዝብ ተሳትፎ ውስጥ የስትራቴጂው አካል መሆን አለበት። የቨርቹዋል ተሳትፎ ዘዴዎች ጥቅም በመጋቢት ወር 2020 በተጀመረው የ “ኮቪድ -19” ወረርሽኝ ወቅት ጎልቶ ታይቷል። ሆኖም፣ ሜትሮ እንደተገቢነቱ እንጂ እንደ ብቸኛው መንገድ አድርጎ ከመውሰድ መጠንቀቅ አለበት። ቴክኖሎጂ እና ሌሎች ዘዴዎችን አደባልቆ መጠቀም ሁሉንም ህዝቦች፣ ምንም ዓይነት ማህበራዊ እና የኢኮኖሚ ሁኔታ ቢኖራቸውም፣ እንዲያካትት ይረዳል። በተለይም ግብረመልስ በሚሰበሰብበት ጊዜ ይህንን ከግምት ውስጥ ማስገባት በጣም አስፈላጊ ነው።

የተደራሽነት መስፈርቶች እና ተገዢነት

ሁሉም የግንኙነት ዕቅዶች ተጽዕኖ የደረሰባቸው ደንበኞች እና የማህበረሰብ ዓባላት የሚፈልጉትን መረጃ ማግኘት እና መሳተፍ እንዲችሉ የሚቀይስዋቸውን መንገዶች ማካተት አለባቸው፡፡

የቋንቋ ድጋፍ ዕቅድ መስፈርቶች

እያንዳንዱ የፕሮጀክት ግንኙነት ዕቅድ መፈጠር ውስን እና ምንም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ለሌላቸው ግለሰቦች ጥቅማ ጥቅሞችን፣ አገልግሎቶችን፣ መረጃዎችን እና አስፈላጊ በሆኑ የሜትሮ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ የሚያረጋግጠውን የሜትሮ የቋንቋ ድጋፍ ዕቅድ (LAP) ማክበር አለበት፡፡ LAP ለግንኙነት እና ለማህበረሰብ ተሳትፎ ፕሮጀክቶች አስፈላጊ ቋንቋዎችን ሲገመግም   የ FTA ን የአራት ምክንያት ትንተና ይመለከታል፡፡

የአራት ምክንያት ትንተና - የቋንቋ ድጋፍ ዕቅድ

በእነዚህ ምክንያቶች እና ውስን እና ምንም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ለሌላቸው (LEP/NEP) የሜትሮ ተሳፋሪዎች ብዛት መሠረት የተመረጠ ቋንቋ (ዎች) በመጠቀም የተወሰነ የግንኙነት ዕቅድ ሲዘጋጅ ተለይቶ የታወቀው ቋንቋ (ዎች) በከፍተኛ ደረጃ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

1. በቋንቋ መረጃዎችን እና አገልግሎቶችን ለማቅረብ እና ከሜትሮ ጋር በሚገናኙበት ጊዜ መረጃውን በተገቢው መንገድ (ማለትም፣ ማንበብ ከማይችሉ ጋር ለመነጋገር) ተመራጭ ቋንቋን መለየት፡፡
2. ውስን ወይም ምንም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ከሌላቸው ሰዎች (LEP/NEP) ከሜትሮ ጋር የሚገናኙበትን ዘዴ መለየት፡፡ በመረጡት ቋንቋ እኩል ተደራሽነት ለመስጠት ቁልፍ መርሃግብሮችን እና አገልግሎቶችን እና ቁልፍ ሠራተኞችን ጥናት እና ግምገማ ማድረግ፡፡
3. ለ LEP/NEP ህዝብ አስፈላጊ አገልግሎቶች እና በጣም ውጤታማ የመግባቢያ ዘዴ በተመረጠው ቋንቋ መለየት እና መገምገም። አስፈላጊ አገልግሎቶችን በተመለከተ ከተለያዩ የሜትሮ አጋሮች፣ ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር መተባበር እና አስተያት ማግኘት፡፡ ለ LEP/NEP ግለሰቦች ምን ዓይነት አገልግሎቶች እና መረጃዎች አስፈላጊ እንደሆኑ ለማወቅ ከተለያዩ LEP/NEP ግለሰቦች ጋር ስብሰባዎችን ማድረግ እና ከሜትሮ አጋሮች እና ማኅህረሰብ ድርጅቶች አስፈላጊውን ትብብር እና አሰተያየት ማግኘት፡፡
4. ያሉትን መረጃዎች እና የተደራሽነት ቁሳቁሶችን መገምገም እና ለ LEP/NEP ግለሰቦች አዳዲስ አስፈላጊ የቋንቋ መረጃዎችን ማዘጋጀት፡፡ በትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ በ LEP/NEP ግለሰቦች፣ ለፖሊሲ ለውጥ የሚሠሩ ቡድኖች እና በመንግሥት ኤጀንሲዎች መካከል የመረጃ አቅርቦቶች ወጪዎችን መገምገም እና ተደራሽ የሆነ መረጃን በንቃት ማጋራት፡፡ ተጨማሪ የተተረጎመ መረጃን ለመጠየቅ በቋንቋ ማሳወቂያዎች አማካኝነት በቋንቋ መረጃ የማግኘት አማራጮችን መስጠት፡፡

የአሜሪካ አካል ጉዳተኞች ሕግ (ADA) ፍላጎቶች እና ተገዢነት

ለአካል ጉዳተኞች እንደሚደረገው ሁሉ፣ የማየት፣ የመስማት ወይም የንግግር እክል ያሉባቸው ሰዎች መረጃን መቀበል እና ማስተላለፍ፣ በአስተያየት የመስጠት ዕድሎች ላይ መሳተፍ እና በዝግጅቶች ላይ መሳተፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ተገዢነትን ለማረጋገጥ የግንኙነት ዕቅዶች የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፣

- በሜትሮ የሚስተናገዱ ሁሉም የዝግጅት ቦታዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው እና ቦታው ከመረጋገጡ በፊት በ ADA ፖሊሲ እና ዕቅድ ቢሮ መገምገም አለባቸው፡፡ ቦታዎቹ በሕዝብ ማመላለሻ ተደራሽ መሆን አለባቸው እንዲሁም በቂ የተሰየሙ የማቆሚያ ቦታዎች ለአካል ጉዳተኛ የሚያመቹ መወጣጫዎችን ጨምሮ እንዲኖራቸው ይገባል፡፡ እንደ የዝግጅቱ ቦታ፣ መወጣጫዎች ወይም የሚሰሩ አሳንሰር አስፈላጊ ሊሆኑ ይችላል፡፡ መጸዳጃ ቤቶች እንዲሁ ተደራሽ መሆን አለባቸው፣ የበር መክፈቻዎች ተመራጭ ናቸው እና በሮች ተገቢ የ ADA በር የመክፈቻ ቦታ (ቢያንስ 32 ኢንች ያለ መተላለፊያ) ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- ለዝግጅቱ ስለሚሰጡ መስተንግዶዎች በጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ በማስተዋወቂያ ሰነዶች፣ በማስተዋወቂያ ሰነዶች ላይ የሚለጠፉ ምልክቶች እና በፕሮጀክቱ የግንኙነት ዝርዝሮች ውስጥ የአከባቢ የአካል ጉዳተኛ ቡድኖች/ድርጅቶች ህብረተሰቡ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት፡፡
- ዝግጅቱን ለመካፈል የሚመጣውን ህዝብ ወደ ቦታው ለመምራት በክፍሎች፣ አሳንሰሮች፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ ተደራሽ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች፣ መወጣጫ ቦታዎች ወይም የተለዩ የማውረጃ ዞኖች ምልክቶች መደረግ አለባቸው፡፡ ለዓይነ ስውራን የአቅጣጫ መረጃ በሚሰማ መልዕክቶች ወይም በሠራተኞች መኖር አለበት፡፡
- የመግባባት ችግር ካለባቸው ሰዎች ጋር ለመግባባት የሚረዱ ረዳት መሣሪያዎች እና አገልግሎቶች መኖር አለባቸው፡፡

ለዕውራን፣ ማየት ወይም መስማት ለተሳናቸው ሰዎች፣ ብቁ የሆነ አንባቢ፣ በትልቁ የህትመት መረጃ፣ በብሬይል ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ በኮምፒውተር ስክሪን ንባብ ፕሮግራም ወይም የታተመ መረጃ በድምጽ ማቅረብ፡፡ በኢንተርኔት/በኤሌክትሮኒክ መንገድ የተለጠፈ ወይም የተጋራ መረጃ ተደራሽ መሆን አለበት፡፡

መስማት ለተሳናቸው፣ የመስማት ችግር ላለባቸው ወይም መስማት-ማየት ለተሳናቸው ሰዎች፣ በዕርዳታ የማዳመጥ መሣሪያ (ዎች)፣ ብቃት ያለው ማስታወሻ-ወሳጅ፣ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ፣ የቃል አስተርጓሚ፣ የ cued-speech አስተርጓሚ ወይም ተቀባይነት ያለው አስተርጓሚ፣ በንንግግሩ ጊዜ ወዲያውኑ የሚደረግ ትሩጉም፣ የጽሑፍ ሰነዶች ወይም የአክሲዮን ንግግር የታተመ ስክሪፕት (ለምሳሌ በሙዝየሙ ወይም በታሪካዊ የቤት ጉብኝት ላይ የተሰጠ)፡፡

የንግግር እክል ላለባቸው ሰዎች፣ ብቃት ያለው የንግግር-በንግግር ቋንቋ ተርጓሚ ያቅርቡ (ግልፅ ያልሆነ ንግግርን ለመለየት እና በግልጽ ለመድገም የሰለጠነ ሰው)፣ ወረቀት እና ብዕር በብቃት ለመነጋገር እንዲችሉ እንደ አጋዥ መሳሪያ ያቅርቡ፡፡

ደረጃ አራት: የመረጃ መስፈርቶችን ማቋቋም

እያንዳንዱ የተስተካከለ የግንኙነት ዕቅድ የበጀት እና የሠራተኛ መረጃዎችን ይጠይቃል። እንደ ዕቅዱ ሂደት CASC ከፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ እና ከፕሮጀክቱ ቡድን ጋር በመሆን በእንቅስቃሴዎቹ እና አስፈላጊ በሆኑ ታክቲኮች የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ይለያል፣

- ***ዕቅዱ የውጭ ሠራተኞች እና ቁሳቁሶች ያስፈልገዋል?*** *የፕሮጀክት ባለቤቶች ወይም ሥራ አስኪያጆች አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች የውጭ ቁሳቁሶች እንደሚያስፈልጋቸው መገመት አለባቸው:: የተለየ ሙያ ያላቸው፣ እንደ ካርታ እና ኢንፎግራፊክ ዲዛይን፣ የቪዲዮ ቀረፃ እና ማስተካከል (editing)፣ የትርጉም/የማስተርጎም አገልግሎቶች፣ የዝግጅት ዕቅድ ማውጣት፣ የብዙ ቋንቋ ተደራሽነት፣ አስፈላጊ ወዋቅሮችን የመገንባት አገልግሎቶች፣ ወዘተ. የሰው ኃይል ከቁሳቁሶች ወይም አቅርቦቶች ከመግዛት ጋር መኖር አለባቸው:: እንደ ፕሮጀክቱ መጠን እና ስፋት የሠራተኛ መጨመር እንደሚያስፈልግ ሊታወቅ ይችላል::*
- ***አስፈላጊ የእገዛ ምንጮችን የማግኘት እና የማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት ማነው?*** የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ አሁን ያሉትን ግንኙነቶች እና ኮንትራቶች በመጠቀም እነዚህን ቁሳቁሶች ለማግኘት በጣም ጥሩ ዘዴዎችን ለመወሰን ከ CASC ጋር አብረው ይሰራሉ:: ሚና እና የኃላፊነት ምደባ ማትሪክስ ወይም ዝርዝር ውስጥ የሚጨመሩ ሲሆን የግዥ ሥራዎች በፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ መጠናቀቅ ሊያስፈልጋቸው ይችላል::

- ***የወጪው መነሻ አስፈላጊ የሆኑትን የቁሳቁስ ፍላጎቶች ያንፀባርቃል?*** CASC *የመጀመሪያ የግንኙነቶች የበጀት* ጅምር አካል ካልሆነ፣ በተጠቀሙት የቁሳቁስ ፍላጎቶች ላይ በመመርኮዝ የወጪው መነሻ ግምገማ ያስፈልገው ይሆናል። የገንዘብ ድጋፍ ምንጭ መረጃ፣ ወጪዎችን ለማጽደቅ ተመራጭ መንገድ፣ ሂሳብ የመጠየቂያ አሠራር፣ ወዘተ… ጨምሮ በፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ መመዝገብ እና መረጋገጥ አለበት:: በበጀቱ ዙሪያ ያሉ ማንኛቸውም ችግሮች ወዲያውኑ መጋራት አለባቸው እና በዕቅዱ እና/ወይም በጊዜ ሰሌዳው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ::

መረጃዎችን ማግኘት እና ማቆየት በተለምዶ በፕሮጀክት የጊዜ ገደብ ላይ ትልቁ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነው:: ተገቢው ዕቅድ ከሌለ ሁኔታው በፕሮጀክቱ ተገዢነት እና የጊዜ ሰሌዳ ላይ በጣም ትልቅ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል::

ደረጃ አምስት: የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት

የግንኙነት ዕቅድ ትግበራ የጊዜ ሰሌዳ በ CASC ከግንኙነት ፕሮጀክት ቡድን ጋር ይዘጋጃል:: የጊዜ ሰሌዳው የሚከተሉትን ግብዓቶች ግምት ውስጥ ያስገባል፣

- በፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ የቀረቡት የስኬት ዝርዝር እና የፕሮጀክት የጊዜ ገደብ/ውጤቶች

- በግንኙነት ዕቅዱ ውስጥ የተገለጹት ተግባራት እና ዘዴዎች ዝርዝር፣ የጊዜ ገደቦችን ጨምሮ

- የውስጥ መረጃዎች መኖር፣ ተጓዳኝ ወይም መጪ ፕሮጀክቶችን፣ በዓላትን እና የእረፍት ጊዜ መርሃግብሮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት

- የውጭ መረጃዎች መኖር፣ ኮንትራት የመስጫ ጊዜዎችን እና ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት

እነዚህ ተግባራት የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎችን ለማጠናቀቅ ከታቀዱ ቀናት ጋር የጊዜ ገደብ ሰሌዳ ሞዴል ለማዘጋጀት በቅደመ ተከተል ይቀመጣሉ:: በበታቀደው መንገድ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ በጠቅላላው የጊዜ ገደብ ሰሌዳ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል::

የጊዜ ገደብ ሰሌዳ ዝግጅት በሚደረግበት ጊዜ ስጋቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል:: ስጋቶቹ እንደ አመራር መመሪያዎች ያሉ ውስጣዊ ስጋቶችን ወይም እንደ አቅራቢ ወይም የውል መዘግየት ያሉ ውጫዊ አንቅፋቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ::

የግንኙነት ዕቅዱ አንዴ ከተረቀቀ በፕሮጀክት ቡድኑ እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ይገመገማል:: እንደ ዕቅዱ ውስብስብነት እና የመረጃ መኖር የዕቅዱ ዝግጅት እና ማጽደቆች እስከ አንድ ወር ሊፈጅ ይችላል::

የፕሮጀክት ጅማሬ

የግንኙነት ዕቅድ ሂደት

የግንኙነት ዕቅድ አፈጻፀም

ቁጥጥር፣ ክትትል እና ሪፖርት ማድረግ

አንዴ ከተጠናቀቀ እና ከፀደቀ፣ CASC እና የግንኙነት ፕሮጀክት ቡድኑ የግንኙነት ዕቅዱን ማከናወን ይጀምራሉ። ለስኬታማ ትግበራ ብዙ ምክንያቶች አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

- ***በፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ እና በ CASC መካከል ተደጋጋሚ እና ግልጽ መግባባት ለፕሮጀክቱ ስኬት ወሳኝ ነው።*** *ይህም የፕሮጀክቱን ወሰን ወይም የጊዜ ሰሌዳን በተመለከተ ማንኛቸውንም ለውጦች ወዲያውኑ ማስተላለፍን እና መደበኛ ዝመናዎችን መስጠትን ያካትታል። CASC የፕሮጀክቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጁ የፕሮጀክት ማዘመኛ ስብሰባዎችን እንዲያስተናግድ ወይም በፕሮጀክቱ ውስጥ አጠቃላይ የጽሑፍ ዝመናዎችን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።*
- *የጊዜ ገደቦች በትግበራ ላይ አለመዋል በፕሮጀክቱ እና በዕቅዱ ሂደት ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖዎች ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ሁሉም ሰው መረዳቱን ማረጋገጥ። አንድ ፕሮጀክት ስኬታማ እንዲሆን ሁሉም የግንኙነት ፕሮጀክት ቡድን ዕቃዎችን በወቅቱ ለማድረስ ተባብረው መሥራት አለባቸው። የአንድ ወይም የሁለት ቀን ማስተላለፍ በፕሮጀክቱ ወሳኝ ሂደት ላይ አንድምታ ሊኖረው ይችላል።*
- *ማንኛውም የወጪ መነሻ እና የመረጃ ዝርዝርን ያካተተ በተፈቀደው የግንኙነት ዕቅድ ላይ የሚደረጉ ለውጦች በለውጥ ቁጥጥር ሂደት መከናወን አለበት። ይህ ማለት ለውጦች በ CASC እና ከመተግበሩ በፊት ተለይተው በሚታወቁ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት መተንተንና መጽደቅ አለባቸው።*
- *ብዙ ወራት ወይም ዓመታት የሚቆዩ የረጅም ጊዜ ፕሮጀክቶች የግንኙነት መንገዶችንን እና መልዕክቶችን በየጊዜው ወይም አንዳንድ ሁኔታዎች እንደተከሰቱ እንደገና መገምገም ያስፈልጋቸዋል። ያልተቋረጠ የባለድርሻ አካላትን ግምገማ እና የህዝብ እርካታ መካተት አለበት።*

በተጨማሪም፣ የግንኙነት ዕቅዱ በተፈቀደው መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ሜትሮ በውጭ የሚመሩ እና በሜትሮ ደንበኞች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ፕሮጀክቶች መደበኛ የሂደት ዝመናዎችን እንዲያቀርቡ ይጠይቃል።

ተገዢነትን ለማረጋገጥ እና ቀጣይነት ያለው መሻሻል እና ግምገማ እንዲኖር ለማስቻል፣ በእያንዳንዱ ፕሮጀክቶች የአፈጻፀም መለኪያ መዋቅር እና የዓንቀጽ 6 መርሃግብር ተገዢነት መሠረት ሁሉም የግንኙነት ዕቅዶች በ CASC ቁጥጥር እና ክትትል ይደረግባቸዋል። የአፈፃፀም መለኪያ መረጃ በአራት ልዩ የሪፖርት ልኬቶች ይሰበሰባል፣

1 የግንኙነት ዕቅዶች

በመገናኛ ዕቅዱ ውስጥ የተዘረዘሩ ብዙ ተግባራት እና ታክቲኮች፣ የዝግጅት ቦታዎችን፣ በቋንቋ አገልግሎት ማግኘት እና የ ADA ተደራሽነትን ጨምሮ በአፈፃፀም መለኪያ ማዕቀፉ ውስጥ ክትትል ይደረግባቸዋል እና በአፈጻጸም መለኪያ መዋቀሩ ይጨመራሉ።

2 እንቅስቃሴ በኋላ ማጠቃለያዎች

እያንዳንዱን የማዳረስ እንቅስቃሴ ወይም ታክቲክ ማጠቃለያ አስፈላጊ ሲሆን የሚከተለውን መረጃ ያካትታል፣

- የእንቅስቃሴ ዓይነት ዓላማ። ይህ እንቅስቃሴ/ታክቲክ ለምን ተመረጠ?
- ግምታዊ/ትክክለኛ ተሳትፎ ወይም መስተጋብሮች። ይህ እንደ የእንቅስቃሴው ዓይነት የተሰበሰቡትን የዳሰሳ ጥናቶች ቁጥር፣ የተሰራጩ ቁሳቁሶችን፣ የተላኩ ኢሜይሎችን ወይም የተሰብሳቢዎችን ወይም የተሳታፊዎችን ብዛት ሊያካትት ይችላል።
- የተመረጠ ስነ-ህዝብ፣ ለምሳሌ፣ አናሳዎች፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ LEP፣ ወዘተ።
- ስርጭት/ማስታወቂያ። ምን ዓይነት የመገናኛ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለው ነበር፣ ቁሳቁሶች የት ተቀምጠው እንደነበር፣ እና ለዚህ እንቅስቃሴ የትኞቹ ቋንቋዎች ታስበው ነበር?
- የእንቅስቃሴው ውጤት። ዓላማው ተሳክቷል?
- ስለ እንቅስቃሴ ዓይነት ወይም ታክቲክ የተገኙ ትምህርቶች።
- የሚመለከተው ከሆነ፣ በዳሰሳ ጥናቶች፣ በአስተያየት ቅጾች ወይም ግምገማዎች ላይ የተደገፉ ውጤቶች።*

3 የድህረ-ፕሮጀክት ግምገማዎች

ሁሉም የተደራሽነት እንቅስቃሴ ማጠቃለያዎች በእያንዳንዱ ፕሮጀክት መጨረሻ ድበህረ-ፕሮጀክት ግምገማ ውስጥ ተካተዋል፡፡

4 የሶስትዮሽ PPP የአፈፃፀም መለኪያ ግምገማ

በዓመቱ ውስጥ የተካሄዱት የድህረ-ፕሮጀክት ግምገማዎች ውጤቶች ዓመታዊ የአፈጻፀም መለኪያ ግምገማ ውስጥ ይካተታሉ። ውጤቶቹ በየሦስት ዓመቱ ሪፖርት ውስጥ ተካትተው የዚህ የሕዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ማሻሻያ አካል ሆነው ይቀርባሉ (ምዕራፍ 3)።

የህዝብ ተሳትፎ አስተዳደር ሥርዓት (PPMS) CASC በመገናኛ ዕቅዶች ላይ ዕድገትን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚጠቀምበት ከውስጥ-የተዘጋጀ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች የፕሮጀክታቸውን ዕድገት ለመከታተል ግልጽነትን ይሰጣል እና ሁሉንም የአሠራር ሪፖርት መለኪያዎችን ለማስገባት ገጽታዎችን ይጨምራል። በተጨማሪም ይህ ሥርዓት መሳሪያ ዒላማዎች መሟላታቸውን የመገምገም ችሎታን ይሰጣል።

የግንኙነት ዕቅዱ ከዋና ባለድርሻ አካላት የቀረበ ጥያቄ ይሁን ወይም በፌዴራል ተልዕኮዎች የሚጠየቁ ማንኛቸውንም ተጨማሪ የግንኙነት ሪፖርቶችን ያካትታል።

በተጨማሪም፣ የግንኙነት ዕቅዱ ፕሮጀክት ከመገናኛ እይታ አንፃር መቼ እንደሚዘጋ ይወስናል። ይህ ሊሆን የሚችለው ሁሉም ሪፖርቶች ሲቀርቡ እና የመጨረሻ ግብዓት ለባለድርሻ አካላት ወይም ለሕዝብ ሪፖርት ሲደረግ፣ ወይም ተፅዕኖው ከተወገደ በኋላ እና የማሳወቂያ ሁኔታዎችን ማንሳት ሲያስፈልግ ሊሆን ይችላል።

** አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ የተደራሽነት እንቅስቃሴዎች ተሳታፊዎች ልምዶቻቸውን መገምገም እና ለአንቀጽ 6 ዓላማዎች አስፈላጊ የሆኑ የስነ-ህዝብ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለሜትሮ ዕድል መስጠት አለባቸው። የዳሰሳ ጥናቶች፣ ግብረመልሶች ወይም የግምገማ ቅጾች ደረጃውን የጠበቀ የአንቀጽ 6 አስተያየት መስጫ ካርድ ቦታን መውሰድ እና ተሳታፊዎች ስለ ርዕሱ ተጨማሪ አስተያየት እና ለወደፊቱ የማዳረስ ሥራዎች ማሻሻያዎችን እንዲሰጡ ዕድል መስጠት አለባቸው።.*

የፕሮጀክት ጅማሬ

የግንኙነት ዕቅድ ሂደት

የግንኙነት ዕቅድ አፈጻፀም

ቁጥጥር፣ ክትትል እና ሪፖርት ማድረግ

ሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዱን የ 2014-2017 አንቀጽ 6 የሦስት ዓመት ክንውን አካል አድርጎ ካወጣ ጀምሮ ባለሥልጣኑ በትራንስፖርት የህዝብ ተሳትፎ ልምዶች ግንባር ቀደም ለመሆን ሰርቷል፡፡ ከሁሉም በላይ PPP ተግባራዊ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ሜትሮ ያስመዘገባቸው በርካታ ፕሮጀክቶች እና ፖሊሲዎች ከህብረተሰቡ ዓባላት በተሰጡ አስተያየቶች ተጠቃሚ ሆነዋል።

ሜትሮ ባለፉት ሦስት ዓመታት በተለይም አቅምን በማሳደግ ሥራ፣ በግንባታ፣ በአገልግሎትና በከፍያ ዋጋዎች ዙሪያ በፕሮጀክት እና በፖሊሲ ተነሳሽነት ከፍተኛ ጭማሪ ነበረው። ይህ ምዕራፍ በህዝብ ግንኙነትና ተሳትፎ ዙሪያ፣ እነዚህን ጥረቶች ለመደገፍ የተቀመጠውን መዋቅር ጨምሮ፣ የተከናወነውን ጉልህ ሥራ ያሳያል።

የፕሮጀክቱ ዓብይ ጉዳዮች

የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ቡድን ከጥር 2018 እስከ መጋቢት 2020 ባለው ጊዜ ውስጥ ከ 60 በላይ ለሆኑ ፕሮጀክቶች የግንኙነቶች እና ተደራሽነት አገልግሎቶችን አስተዳድሯል። ከዚህ በታች አዳዲስ የግንኙነቶች እና የተሳትፎ ቴክኒኮችን ተግባራዊ ያደረጉ የሁለት ፕሮጀክቶች ማጠቃለያዎች ቀርበዋል። የተሟላ የፕሮጀክቶች ዝርዝር በአባሪ መ: የአገልግሎት እንቅስቃሴ ዝርዝር ውስጥ ይገኛል።

የ 2021 ዓመታዊ በጀት

በየክረምቱ ሜትሮ ለመጪው የበጀት ዓመት ጠንካራ የህዝብ ግብዓት ሂደት ያጠናቅቃል። ለ 2021 የታቀደው በጀት የደንበኞችን ተሞክሮና የዋጋ አማራጮችን ለማሻሻል እና ወጪዎችን ለማስተዳደር ነው። 11 የታቀዱ የዋጋ ለውጥ እና ሰባት የታቀዱ የአገልግሎት ለውጦችን አካቷል።

የግንኙነት ዕቅዱ በጣቢያዎች የተደራሽነት ዝግጅቶች፣ በትራንስፖርት ማዕከላት እና በአውቶብስ ማቆሚያዎች፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ልዩ ማስታወቂያዎች እና ሚዲያዎች፣ ለህዝብ ክፍት የሆኑ ዝግጅቶች እና ኮምፓክት (Compact) የህዝብ ችሎቶችን የመሳሰሉ መደበኛ ታክቲኮችን አካቷል። ሆኖም በቀረቡት የውሳኔ ሃሳቦች ውስብስብነት እና ብዛት የተነሳ የደንበኞችን ግንዛቤ ለማሳደግ እና የበለጠ ገንቢ ምላሾችን ለመቀበል አዳዲስ መሳሪያዎችና ዘዴዎች አስፈላጊ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

- የበጀቱ አካል የነበሩትን ሀሳቦች ሁሉ በትክክል ለመሸፈን (18 ምድቦች፣ በድምሩ ለ 100 የተለያዩ ሀሳቦች) የኦንላይን የዳሰሳ ጥናት መሳሪያ ግብረመልስ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውሏል። ምንም እንኳን የዳሰሳ ጥናቱ የተስተካከለ ቢሆንም ደንበኛው ግብረመልስ ለመስጠት በመረጡት ሀሳቦች ላይ በመመርኮዝ ለማጠናቀቅ ቢያንስ ከአምስት እስከ 10 ደቂቃዎችን ይፈልጋል። በፕሮፖዛሉ ውስብስብነት ምክንያት የወረቀት ዳሰሳ ጥናት መፍጠር አማራጭ ስላልነበረ የኦንላይን ተሳትፎን ለማበረታታት ለጎዳና ተደራሽ ቡድኖችን አዳዲስ መሳሪያዎች ተፈጥረው ነበር።
- በህዝብ አስተያየት ወቅት ከ 106,440 በላይ በራሪ ወረቀቶች በጎዳና አሰራጭ ቡድኖች ተሰራጭተዋል። ብሮሸሮቹ የእንግሊዝኛ እና የስፓንሽኛ ቋንቋ ያካተቱ ሲሆን፣ በመረጡት ቋንቋ መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በአማርኛ፣ በቻይንኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በኮሪያንኛ እና በቬትናምኛ ቋንቋዎች እና ደንበኞች ከሞባይል ሰልካቸው በቀጥታ ወደ ዳሰሳ ጥናቱ ለመሄድ የሚያስችል የ QR ኮድ አካቷል። ጽሁፎቹ በተጨማሪ በዳሰሳ ጥናቱ ላይ የሚካፈሉ የማበረታቻ የ 50 ዶላር SmarTrip® ካርድ የማግኘት ዕድል እንደሚኖር አስታውቀዋል፡፡
- የብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ተደራሽ ቡድኖች በዕርዳታ አሰጣጥ ዝግጅቶች ወቅት ታብሌቶችን ይይዛሉ። የዳሰሳ ጥናቱን ለመውሰድ ፍላጎት ያሳዩ ደንበኞች ጥናቱን በቦታው መውሰድ ይችላሉ፣ ሆኖም፣ ዳሰሳውን ለመውሰድ ጊዜ የሌላቸው በፍጥነት የመገናኛ መረጃን በማቅረብ የዳሰሳ ጥናቱን በቀጥታ በኢሜል ወይም በቴክስት በእንግሊዝኛ እና ስፓንኛ ቋንቋዎች እንዲላክላቸው ማድረግ ይችላሉ።

- ለመጀመሪያ ጊዜ የኦንላይን የክፍያ ማስሊያ መሣሪያ በሜትሮ ሠራተኞች ተሠራ። ይህ መሣሪያ በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽኛ ቋንቋ የሚሠራ ሲሆን ደንበኛው ጉዞ ሲጀምር መክፈል የሚኖርበትን አሁን ካለው ዋጋ ጋር ለማስላት ያስችለዋል። የተለያዩ የዋጋ ፐርፖዛሎች ሊለዋወጡ የሚችሉ ሲሆን መሣሪያው የትኛው መተላለፊያ ገንዘቡን መቆጠብ እንደሚችል ሊረዳው ይችላል። ወደ ማስሊያው የሚያስገባው ሊንክ በድህረ ገፁ ላይ እና በተደራሽ ቡድኖች ታብሌት ላይ ይገኛል፡፡ ድህረ ገፁ ከ 2500 ጊዜ በላይ ተጎብኝቷል፣ ከነዚህም 2200 በላይ የሚሆኑት አዲስ ጎብኝዎች ናቸው።

እነዚህ ጥረቶች ሜትሮ በጀቱ ላይ ከ 17,000 በላይ ምላሾችን እንዲሰበስብ አግዘዋል፣ 93 በመቶው በዳሰሳ ጥናቱ በኩል የተገኙ ናቸው።

መስመር 79 ሜትሮኤክስትራ (MetroExtra) ከጥሬ ገንዘብ ነፃ የሙከራ ጥናት

በአውቶቡሶች ላይ የጥሬ ገንዘብ ልውውጥን ማስወገድ በአሠራር እና በደንበኞች ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖዎች ለማወቅ በሰኔ 2018 በ መስመር 79 ሜትሮኤክስትራ (Route 79 MetroExtra) ላይ አንድ ዓመት የወሰደ የሙከራ ጥናት ተካሂዶ ነበር። መስመሩ ለሙከራ ጥናት በብዙ ምክንያቶች ተመርጧል፣ በተለይም የ SmarTrip® የግዥ እና የመጫን አማራጮች መዋቅር በየኮሪደሩ በመገኘታቸው ነው፡፡

የሙከራ ጥናቱ ዓላማ በእርግጥ የተጠበቁት አገልግሎቶች መተግበር መቻላቸውን ለመገምገም ነበር፡፡ይህም የሚያጠቃልለው ደንበኞች የሙከራ ጥናቱን ይፈልጉ እንደሆነ፤ በደንበኞች ወይም በኦፕሬተሮች ላይ ከባድ ሸክም ይጨምር እንደሆን እና ከጥሬ ገንዘብ ነፃ መሳፈሪያ መንገዱ ምን ዓይነት የአሠራር ችግር እንደሚፈጥር ወይም የአገልግሎት አፈፃፀምን እንደሚያሻሽል ለማወቅ ነው፡፡ ሠራተኞች ደንበኞችን ለማስተማር እና ለአፈፃፀም እርምጃዎች የሚያስፈልገውን ግብዓት ለመሰብሰብ እንደ የግንኙነት ዕቅዱ አካል አዲስ ታክቲኮች ተጠቅመዋል፡፡

- የአውቶቡስ ኦፕሬተሮች ከሙከራ ጥናቱ ጋር ስላላቸው ልምድ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ ደንበኞች “ያለ ጥሬ ገንዘብ ክፍያ” በሚለው ቃል ከክፍያ ነፃ መስሏቸው ግራ መጋባታቸውን የገለጹ ሲሆን፣ ይህም ለወደፊቱ የግንኙነት እና የመልዕክት ማስተላለፍ ዘዴዎች ውሳኔ ላይ ትምህርት መስጠት አለበት በማለት አስተያየታቸውን ሰጠተዋል፡፡

- የሙከራ ጥናቱ በደንበኞች ግዝቤ እና ባህሪ ላይ ያስከተለውን ውጤት ለመለካት በመስመር 70 እና 79 ሜትሮኤክስትራ መስመር በሙከራ ጥናቱ ላይ ለሦስት ወራት ያህል በተሳፋሪዎች በተካሄደው የዳሰሳ ጥናቶች 1200 ምላሾች ተገኝተዋል፡፡ ከተለመደው አመቺ ናሙና ይልቅ በ 70 እና በ 79 መስመሮች ላይ በሥራ ቀን የሜትሮአውቶቡስ ተሳፋሪዎችን የሚወክል ናሙና መኖሩን ለማረጋገጥ እና “መደበኛው” ደንበኛ በፖሊሲው ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳደረሰበት ለማረጋገጥ ጠበቅ ያለ የናሙና ዕቅድ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ ውጤቶቹ እንደሚያመለክቱት ተሳፋሪዎች የሙከራ ጥናቱን የሚደግፉ እና የጉዞ እና የመቆያ ጊዜዎች መሻሻሎችን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ተሳፋሪዎች የሙከራ ጥናቱ የSmarTrip® ካርድ የመጫን ልምዶቻቸውን እንዲቀይሩ እንደገፋፋቸው ገልፀዋል፡፡

- የሙከራ ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት የብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ተደራሽ ቡድኖች ስለ የሙከራ ጥናቱ ለማሳወቅ ብዙ ተሳፋሪ ወደ አለባቸው የአውቶቡስ ማቆሚያዎች ሄደው ነበር፡፡ ቡድኖቹ ትኩረት የሰጡት ደንበኞች SmarTrip® ካርዶቻቸውን በተለያየ መንገድ እንዴት መጫን እንደሚችሉ ማስተማር እና በጥሬ ገንዘብ ከመክፈል ይልቅ ይሄኛውን መንገድ መጠቀሙ የሚሰጠውን ጥቅም ማስተማር ላይ ነበር፡፡ በመስመሩ ላይ ያሉ የ SmarTrip® መግዣ እና መሙያ ቦታዎችን ያካተቱ በግምት ወደ 10,000 ብሮሹሮች ተሰራጭተዋል፡፡

ሜትሮ በመጨረሻ ከጥሬ ገንዘብ ነፃ ፖሊሲን ተግባራዊ ላለማድረግ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ ሆኖም ይህ ግብዓት በአውቶቡስ የዋጋ ፖሊሲዎች ላይ ወደፊት ለሚደረጉ ውይይቶች ተጨማሪ መመሪያን ሰጥቷል፡፡

ሌሎች መታሰብ የሚገባቸው ፕሮጀክቶች:

- የፕሮጀክቱ የግንኙነት ዕቅድ የመድረክ ማሻሻያ ቀድሞ ከታቀዱት የመዝጋት ዕቅዶች የተስፋፉ ሲሆን ግላዊ የኦንላይን የጉዞ አማራጮች ዕቅድ፣ የፕሮጀክት ብሎግ እና የየሁለት ሳምንት የግንባታ ለውጦችን አካቷል፡፡ ተጽዕኖ የሚታይባቸው ማህበረሰቦች ላይ ለማተኮር ቡድኑ የ Nextdoor (ሃይፐር-ሎካል ማህበራዊ ሚዲያ ኔትወርክ) አጠቃቀምን በተሳካ ሁኔታ መርምሯል፡፡
- የዌስት ሀያትስቪል ኮንክሪት እና ፔቭመንት ጥገና ፕሮጀክት የግንኙነት ዕቅድ ያተኮረው ጣቢያውን የሚጠቀሙት ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው ደንበኞች ቁጥር በርካታ በመሆኑ በተለያዩ ቋንቋዎች መረጃን ማቅረብ ላይ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ሁሉም የተደራሽ ቡድን ዓባላት ባለሁለት ቋንቋ የስፓንሽኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሲሆኑ፣ ከስድስት ፈረቃዎች በላይ ከ 2300 በላይ ግንኙነቶች አጠናቀዋል፡፡
- የአውቶብስ ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት ከባለድርሻ አካላት ጋር ሁሉን ህብረተሰብ የሚያካትት የቡድን እና የኮሚቴ ስብሰባዎች፣ ስዎች ባሉበት ስፍራ በመሄድ የሚካሄዱ ስብሰባዎች፤ ለህዝብ ክፍት የሆኑ ዝግጅቶችን፣ እንዲሁም የአውቶቡስ ኦፕሬተሮች/ሹፌሮችን ያተኮረ የጋራ ውይይቶች በስትራቴጂ እና ድርጊት መርሃ ግብር ላይ ግብረመልስ ለመስጠት የሚያስችል ለሚቀጥሉት አሥር ዓመታት የሚቆይ ክልላዊ፣ ሁሉን አቀፍ የግንኙነት ዕቅዶችን ገንብቷል፡፡ ሁለት የህዝብ ጥናቶች ከ 8,800 በላይ ምላሾችን አግኝተዋል ፡፡

ስለ እነዚህ ፕሮጀክቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወይም ማንኛውንም የህዝብ ግንኙነት እና ግብዓት ሪፖርት ቅጅ ለማግኘት የይዘት እና ስትራቴጂ ግንኙነት ቢሮን ያነጋግሩ፡፡

የሜትሮ ሠራተኞች የህዝብ ተሳትፎ አስተዳደር ሥርዓት (PPMS) ተብሎ በሚጠራው በተለይ ለግንኙነት ዕቅዶቻቸው ሂደት በተቀረፀ በድህረ ገፅ ላይ የተመሠረተ የክትትል መሳሪያ ይጠቀማሉ። ይህ መሳሪያ የታቀዱ ፕሮጀክቶች የህዝብ ተሳትፎን ለመከታተል አዲስ መንገድ ይፈጥራል እንዲሁም በቀላል ሪፖርት ለማድረግ አንድ ትልቅ የመረጃ ቋት ይፈጥራል፡፡ PPMS በትራንስፖርት ውስጥ የህዝብ ተሳትፎን ለመከታተል ብቸኛው መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

የህዝብ ተሳትፎ አስተዳደር ሥርዓት ለተጠቃሚዎቹ ለእያንዳንዱ መምሪያ ፕሮጀክቶች የግንኙነት ዕቅዶችን በሰነድ በማስመዝገብ፣ ስለ ተደራሽነት እንቅስቃሴ ውጤቶች መረጃዎችን በመያዝ እና ዓመታዊ የፌዴራል ትራንስፖርት አስተዳደር (FTA) የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች፣ በአባሪ መ፡ የተደራሽነት እንቅስቃሴ ዝርዝር የተጠቀሰውን፣ ሪፖርት በድህረ ገፅ አማካይነት ይሰጣቸዋል፡፡ PPMS የተፈጠረው ለሁለቱም የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች እና የይዘት እና ስትራተጂ ግንኙነት ጽ/ቤት ተጠያቂነትን እና ስለ ፕሮጀክቱ እና የዕድገት ክትትል መረጃ ለመስጠት ነው። ለሁሉም የውስጥ ሜትሮ ተጠቃሚዎች በሥልጣኑ ኢንትራኔት፤ በሜትሮዌብ በኩል ይገኛል።.

ከ PPMS ቁልፍ ተግባራት አንዱ የአፈፃፀም እርምጃዎችን የመከታተል ችሎታ ነው፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥጥር፣ ክትትል እና ሪፖርት ማድረግ ክፍል እንደተገለጸው በ PPMS ውስጥ የግንኙነት ዕቅዶችን፣ ከእንቅስቃሴ በኋላ ማጠቃለያዎችን እና ከፕሮጀክት በኋላ ግምገማዎችን ጨምሮ በርካታ የሪፖርት ልኬቶች መከታተያ መንገዶች አሉ። በጥር 2018 እና መጋቢት 2020 (ከወረርሽኙ በፊት) መካከል በተጠናቀቁት ግብዓቶች መሠረት የሜትሮ የሦስት ዓመት PPP አፈፃፀም መለኪያ ግምገማ ከዚህ በታች ይገኛል።

ስትራተጂ	ድርጊት	የአፈፃፀም መለኪያዎች፣ ዒላማዎች እና መነሻዎች
1. ዘዴዎች እና መረጃ		
የፕሮጀክቱን ታዳሚዎችን (አነስተኛ ወይም ምንም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ለሌላቸው፣ አነስተኛ ገቢ ለሚያገኙ እና ሌሎች አናሳ ህብረተሰቦች) ለማሳተፍ ምን ዓይነት እርምጃ ተወስዷል?	የተደራሽነት ዝግጅቶች ለተሳታፊዎች በአካል ተደራሽ ናቸው::	1. የተደራሽነት እንቅስቃሴዎች 100% ከሜትሮአውቶብቡስ ወይም ከሜትሮባቡር መስመር በ 1/4 ማይል ውስጥ ነበሩ።
		2.ለተደራሽነት ዝግጅት የሚሆኑ ቦታዎች 100% በ WMATA ADA ሠራተኞች ጸድቀዋል::
	የእንቅስቃሴ መረጃዎች፣ ማርኬቲንግ እና የማስተዋወቂያ ቁሳቁሶችን ጨምሮ ለተሳታፊዎች ተደራሽ ናቸው።	3. 99.95% የተደራሽነት ቁሳቁሶች በፕሮጀክት ግንኙነት እና በተደራሽነት ዕቅድ በተለዩት ሁሉም ቁልፍ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል።
		4.**45.68%** የሚሆኑት እንቅስቃሴዎች መረጃዎችን ለማስተዋወቅ ብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚጠቀሙበትን ሚዲያ ተጠቅመዋል።
		5.**97.34%** የተደራሽነት ቁሳቁሶች ዝግጅቱ ከመድረሱ ቢያንስ ሁለት ሳምንት በፊት ተዘጋጅተው ነበር።
2. ተሳትፎ እና የመርሃ ግብሩ ግብረመልስ		
የተሣታፊነት መጠን ከፕሮጀክቱ ስነ-ህዝብ ስርጭት ጋር ይመሳሰላል? ህብረተሰቡ እና ሠራተኞቹ ተደራሽነቱን ውጤታማ አድርገው ተመለከቱት?	ለአነስተኛ ቡድኖች ከተዘጋጁ ስብሰባዎች ውጭ የፕሮጀክት ተደራሽነት ዝግጅቶች ደህና ተሳታፊ ይኖራቸዋል።	6. **97.95%** የተደራሽነት እንቅስቃሴዎች ለዚህ ዓይነት ዝግጅት ተሳታፊ የመገኘት ግብን አሟልተዋል።
	በተደራሽነት የ LEP፣ አናሳ እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ተሳትፎ ትክክለኛውን የፕሮጀክቱን ስነህዝብ ያሳያል።	7. **99.59%** አናሳ እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቡድኖች በተደራሽነት እንቅስቃሴ ደረጃ በፕሮጀክት ግንኙነት እና ተደራሽነት ዕቅድ ውስጥ የተካተቱት የስነ-ህዝብ ብዛትን አሟልተዋል ወይም አልፈዋል።
	የተደራሽነት ዝግጅት ተሳታፊዎች አዎንታዊ ተመክሮ የነበራቸው ሲሆን ግብዓት ለማቅረብ በሚረዱ ዕድሎች ረክተዋል።	8. **100%** የተደራሽነት እንቅስቃሴዎች ከዝግጅት-በኋላ አስተያየት ካርድ ወይም ለእያንዳንዱ የፕሮጀክት እንቅስቃሴ የዳሰሳ ጥናት አማካይ ‹ጥሩ› ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ደረጃዎችን አግኝተዋል።
	ከተደራሽነት ሂደት የተገኙ ቁልፍ ትምህርቶች	9. 75.65% የተደራሽነት እንቅስቃሴ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጆች ለወደፊቱ ተደራሽነት የተማሩትን ቁልፍ ትምህርቶችን አጠቃለዋል።
3. ክትትል		
ለሁሉም የህዝብ ተደራሽነት ተስታፊዎች ስለ ፕሮጀክቱ የመከታተያ መረጃ፣ የማስፈጸም አስተያየቶችን እና ዕቅዶችን ጨምሮ፣ ግልጽ የሆነ ዕድል መስጠት።	ሁሉም የተደራሽነት ተሳታፊዎች ስለ ዝግጅት ውጤቶች፣ የፕሮጀክት ውጤቶች እና አፈፃፀም ይነገራቸዋል::	10. ለ **100%** የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ቁልፍ የሆኑ ምክሮችን ከሕዝብ ጠቅለል አድርጎ በማብራራት እነዚህ ለምን ሊተገበሩ እንደማይችሉ አስረድቷል::
		11. ለ **100%** የተደራሽነት እንቅስቃሴዎች ምክሮች/ውጤቶች የመገናኛ መረጃቸውን (ግንኙነት ለማድረግ የጠየቁ) ለሰጡ ተሳታፊዎች እና ባለድርሻ አካላት/ለማህበረሰብ ድርጅቶች ተላልፈው ነበር።
		12. **91.48%** በፕሮጀክት ዕቅድ እና ትግበራ መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከድርጅት ተሳታፊዎች እና ከባለድርሻ አካላት/ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ለመገናኘት የሚያስችል አሰራር ሲኖር 91.48%
		13. ለ **99.06%** በፕሮጀክቱ አፈጻጸም የተደራሽነት እንቅስቃሴዎች ህዝቡን እንደገና ለማሳወቅ (ከፕሮጀክቱ ቁልፍ የስነ-ህዝብ ቡድኖችንም ጨምሮ) ግልጽ የሆነ ሂደት አለ።

ከደንበኞች እና ከህዝቡ ግብረመልስ በስፋት መሰብሰብ ሜትሮ ተሳፋሪዎችን በተሻለ ሁኔታ እንዲያገለግል ያስችለዋል። የደንበኞች ምርምር ጽሕፈት ቤት የተሻሉ የንግድ ሥራ ውሳኔዎችን ለማድረግ አስተዋይ ግብዓት በሚሰበስቡ በርካታ ፕሮጀክቶች ላይ ይሠራል። አንዳንዶቹ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን አካትተዋል፣

- በተለያዩ የመከታተያ ልኬቶች ላይ ስኬታማነትን ለመለካት በየሦስት ወሩ የሜትሮ ደንበኞች እርካታ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ።
- በታቀደው የዝቅተኛ-ገቢ ክፍያ ላይ ግብረመልስ ለመሰብሰብ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ደንበኞች አንድ ለአንድ ቃለ-መጠይቆች ማካሄድ እና የአፈጻጸም እና የክፍያ አቅርቦት ጥቅምን እና አጠቃቀም በተመለከተ የውስጥ ውሳኔዎችን ማስተማር።
- የአዳዲስ ሜትሮአውቶቡስ ዲዛይን እና አቀማመጥን፣ አዲሶቹ አውቶቡሶች የመንቀሳቀሻ መሳሪያ ለሚጠቀሙ የሜትሮአክሰስ ተሳፋሪዎች ጠቃሚነታቸውን ጨምሮ፣ በተመለከተ የትኩረት ቡድኖችን ማካሄድ።
- ከኮቪድ -19 በኋላ ወደ ሜትሮ ሲስተም መመለስን በተመለከተ የደንበኞችን ስጋት ለመለየት እና መፍትሄ ለማቅረብ የሜትሮባቡር እና የሜትሮአውቶቡስ ደንበኞች የኦንላይን የትኩረት ቡድኖችን እና የኦንላይን የዳሰሳ ጥናቶችን ማካሄድ።
- በኮሎምቢያ ፓይክ በአውቶቡስ ማቆሚያዎች በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ የኤሌክትሮኒክስ ማሳያዎችን ያሰማራ የሙከራ ፕሮጀክት ስኬት ከሜትሮቡስ ደንበኞች ግብረመልስ በመሰብሰብ፤ ይህም ደንበኞች የአውቶቡስ ማቆሚያዎች የኤሌክትሪክ ግንኙነቶች ባይኖራቸውም እውነተኛ የሜትሮቡስ መረጃን በወቅቱ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።
- በጣቢያ እና ሲስተም ጥገና መዘጋት ወቅት በሜትሮ ለሚደረጉ ተተኪ የሻትል አገልግሎቶች የፍላጎት ግምቶችን እንዲሰጡ ደንበኞችን መጠየቅ።
- የሜትሮ ፓርክ እና ራይድ ደንበኞች የዳሰሳ ጥናት የተለያዩ የጉዞ ሞዶችን ተወዳዳሪነት ለመለየት እና የጣቢያ ተደራሽነትን ለማሳደግ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን የሚደግፉ ሰፈሮችን ለመለየት እና ባለድርሻ አካላት በስልጣን ላይ ላሉት አጋሮች መሻሻል ሀሳብ እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል፡፡

የማህበረሰብ ድርጅት (CBO) ተሳትፎ የታቀዱ ፕሮጀክቶች የግንኙነት ዕቅዶች ወሳኝ አካል ሆኖ ቀጥሏል። በእኩል የሥራ ስምሪት ዕድል ጽ/ቤት የሚተዳደሩት እነዚህ ግንኙነቶች በፕሮጀክት ውሳኔዎች ላይ ጠቃሚ ግንዛቤን ሰጥተዋል። መጠነ ሰፊ የተሳትፎ ጥረቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

- **የአውቶብስ ትራንስፎርሜሽን ጥናት፣- 2018-2019:** ጥናቱ የተለያዩ ክልላዊ አመለካከቶችን እና በአውቶብስ ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ጉዳዮች ላይ ወሳኝ ግንዛቤን የሚሰጡ፣ በአከባቢ እና በክልል መንግስታት ውስጥ በአመራር ቦታዎች ያሉ፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የንግድ ድርጅቶች ፣ አናሳ እና የአካል ጉዳተኛ ቡድኖች ፣ የሠራተኛ ድርጅቶች፣ የአስተሳሰብ ተቋማት እና የትምህርት ማህበረሰብ ዓባላት የተካተቱበት የስትራተጂ አማካሪ ፓነል አካቷል።
- **የሰማያዊ /ብርቱካንማ/ሲልቨር መስመር አቅም እና አስተማማኝነት ጥናት፣- 2019-እስከ አሁን:** ይህ ቀጣይ ጥናት በጥናቱ አካባቢ የሚገኙ የንግድ ቡድኖች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮችን ያቀፈ የንግድ እና የማህበረሰብ አማካሪ ኮሚቴን ያካተተ ነው፡፡ በቅድመ-ጽንስ ሀሳቦች ላይ ግባዓት ለመሰብሰብ በጥቅምት ወር 2019 የ ማህበረሰብ/የንግድ ባለድርሻ አካል ወርክሾፕ ተካሂዷል።
- **የሌሊት እና የጧት እንቅስቃሴ ጥናት -2019 እስከ አሁን-** በክልሉ የሚገኙ የማህበረሰብ ድርጅቶች ባለድርሻ አካላት የትኩረት ቡድኖች የለሊት እና የጥዋት መተላለፊያ በመጠቀም መራጮቻቸው የሚያጋጥማቸውን እክል እና ቅድሚያ የሚሰጡባቸው ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ተጋብዘው ነበር። የትኩረት ቡድኖች በሰኔ 2020 በኦንላይን ተስተናግደው ነበር።

የማህበረሰብ ድርጅቶች የሚከተሉትን ጨምሮ በሌሎች በርካታ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ላይ ግብዓት እንዲያቀርቡ ተጠይቀዋል፣ የበጀት ዓመቱ በጀቶች፣ በ R1, R2,42,43 መስመሮች የአውቶቡስ ጥናቶች፣ የብሌድዴንስበርግ አውቶቡስ ጋራዥ መልሶ ግንባታ፣ የፔንሲ ድራይቭ ከባድ ጥገና እና የህንፃ ማሻሻል፣ በተወሰነ-ማቆሚያ የሜትሮባቡር መስመሮች ላይ ጥሬ ገንዘብ ክፍያን ማስወገድ፣ የ W9 መስመርን ማስወገድ፣ እና የዲንውድ ሜትሮባቡር ጣብያ ህንጻዎች ላይ ለውጦች ማድረግና ሌሎችም ለውጦች ተደርገዋል። በተጨማሪም፣ የማህበርሰብ ድርጅቶች የጣቢያ እና የመግቢያ መዘጋቶች፣ አገልግሎት፣ ክፍያ ወይም የመኪና ማቆሚያ ለውጦች እና ግንባታን ጨምሮ ስለ ሌሎች ተጽዕኖዎች እንዲያውቁ ተደርጓል።

ሜትሮ የአካባቢ ባለድርሻዎች፣ ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲዎች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች የተውጣጡ ተወካዮችን የሚያካትት የግንኙነት መረጃ የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ይጠቀማል። የመረጃ ቋቱ በሠራተኞች መሻሻሉ የቀጠለ ሲሆን ስለነዚህ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ለመግባባት ጥቅም ላይ ይውላል፡

ሜትሮ በሁሉም የታቀዱ የፕሮጀክት የግንኙነት ስትራቴጂዎች ውስጥ የቋንቋ ድጋፍ ዕቅድ መከተሉን የቀጠለ ሲሆን እነዚህን ጥረቶች ለመደገፍ የሚያስችሉ አሠራሮችንም ዘርግቷል፡፡

በአካል ተደራሽነት

ሜትሮ ለተለያዩ ፕሮጀክቶች የህዝብ ተሳትፎ ድጋፍን የሚሰጥ የጥሪ ማሰራጫ ውል ይጠቀማል፡፡ ውሉ በፕሮጀክቱ ፍላጎቶች ላይ የተመረኮዘ፣ በጾታ፣ በዘር፣ በብሔር እና በሚነገሩ ቋንቋዎች ላይ የተመሠረተ የግለሰቦችን ሙያዊ ቡድኖችን ለመፍጠር ተለዋዋጭነትን ይሰጣል፡፡ የቋንቋ ፍላጎቶች አማርኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኮሪያኛ፣ እስፓኝ፣ ቬትናምኛ ወይም የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (ASL) ያካትታሉ፣ ግን አይወሰኑም፡፡ ሁሉም የማዳረሻ ቡድኖች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በቋንቋ እርዳታ በሚሰጠበት መስመር ጋር ለመገናኘት ወደ ሜትሮ የደንበኞች መረጃ ቢሮ ለመደወል የሰለጠኑ ናቸው፡፡

ከ ጥር 2018 እስከ መጋቢት 2020 (ቅድመ-Covid-19)፣ ይህ ውል ለሚከተሎት ጥረቶች ጥቅም ላይ ውሏል።

የጥሪ ውል የማዳረስ ቡድን ፕሮጀክቶች	የጊዜ ሰሌዳ	የተደራሽነት ዓይነት	ባለ ሁለት ቋንቋ ሠራተኞች*
የመኪና ማቆሚያ ፓይለት ፕሮጀክቶች	ጥር- የካቲት 2018	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኝ (50%)፣ ቻይንኛ
የግሮንስብርግ መመለሻ ማስወገጃ ፕሮፖሳል	ግንቦት 2018	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት	ስፓኒሽኛ (50%)፣ ቻይንኛ
የአውቶቡስ አገልግሎት ለውጦች	ሰኔ 2018	ስለ አገልግሎት ለውጦች ለደንበኞች ማሳወቅ	ስፓኒሽኛ (50%)
የምዕራብ ሀያትትስቪል ኮንክሪት እና የድንጋይ ንጣፍ ጥገና	ግንቦት-ሃምሌ 2018	ስለ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች መዘጋት ለደንበኞች ማሳወቅ	ስፓኒሽኛ (100%)
መስመር 79 ሜትሮኤክስትራ ከጥሬ ገንዘብ ነፃ ሙከራ	ሰኔ 2018	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታትየዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ (100%)
የሜትሮባቡር ጣቢያ ደንበኞች አገልግሎት (MLB All-Star Game)	ሀምሌ 2018	በጣቢያዎች ውስጥ ደንበኞችን ይረዱ	ስፓኒሽኛ (50%)
የፍሬንድሺፕ ሃይትስ ቤይ ግንባታ	ሀምሌ-ነሀሴ 2018	ስለ ተዘዋወሩ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች ለደንበኞች ማሳወቅ እና ማገዝ	ስፓኒሽኛ (50%)
የትራዘመው የቀይ መስመር መዘጋት	ሀምሌ-ነሀሴ 2018	በጣቢያዎች መዘጋት ለደንበኞች ማሳወቅ እና ማገዝ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ፣ አሜሪካን የምልክት ቋንቋ (ASL)
ሰማያዊ/ብርቱካንማ/ሲልቨር መአስመር የተራዘመ ነጠላ--ሀዲድ	ሀምሌ-ነሀሴ 2018	ስለ አገልግሎት ለውጦች ለደንበኞች ማሳወቅ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ፣ ኮሪያንኛ
ከከጥሬ ግንዘብ-ነፃ የተወሰነ የአውቶቡስ ማቆሚያ ፕሮፖዛል	September 2018	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት፣ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ፣ ቻይንኛ
የመኪና ማቆሚያ ለውጦች እና ልይ ዝግጅቶች ፕሮፖዛል	ጥቅምት 2018	በቀረብ ሃሳቦች ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት፣ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ፣ ቻይንኛ፣ ኮሪያንኛ
ሰማያዎ/ቢጫ መስመር የተራዘም የሰንበት መዘጋት	ህዳር 2018	ስለ ጣቢያዎች መዘጋት ለደንበኞች ማሳወቅ እና ማገዝ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ
ቪየና እና ላራጎ ታውን ሴንተር የማኪና ማቆሚያ ምመልሶ ማቋቋም	ህዳር 2018	ስለ የመኪና ማቆሚያ ቦታ መዘጋት ለደንበኞች ማሳውቅ	ስፓኒሽኛ (50%)
ቢጫ መስመር አይኖርም	ህዳር 2018	ስለ አገልግሎት ለውጦች ለደንበኞች ማሳወቅ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ፣ ቻይንኛ
ሪግስ ሮድ (R1, R2 መስመሮች) የአገልግሎት ግምገማ ጥናት	ህዳትር 2019	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታጣት፣ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ (50%)
ሜትሮባቡር ጣቢያዎች ደንበኞች አገልግሎት፡ የሴቶች ዓመታዊ ሰላማዊ ሰልፍ	ጥር 2019	በጣቢያዎች ውስጥ ደንበኞችን መርዳጥ	ስፓኒሽኛ (50%), አማርኛ፣ ቻይንኛ ኮሪያንኛ
የ 2020 የበጅት ዓመት በጀት	ጥር 2019	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት፣ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ፣ ቻይንኛ፣ ኮሪያንኛ
የሜትሮ ለውጥ ቀን: የማለፊያ ቁሳቁሶች	ሀምሌ-መስከረም 2019	ስለ አዲስ ማለፊያዎች ለደንበኞች ማሳወቅ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ
የሜትሮአውቶቡስ ጥሩ አሠራሮች ሁኔታ	መስከረም 2019	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት፣ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ
የፐርፐል መስመር ለኒው ካሮልቶን ባቡር ጣቢያ ተጽዕኖዎች	ህዳር 2019	ስለ የመኪና ማቆሚያ ቦታ መዘጋት ለደንበኞች ማሳወቅ	ስፓኒሽኛ (50%)
የፐርፐል መስመር ለሲልቨር ስፕሪንግ የትራንስፖርት ማዕከል ተጽዕኖዎች	ታህሳስ 2019- ጥር 2020	ስለ ተዘዋወሩ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች ለደንበኞች ማሳወቅ እና ማገዝ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ
የ 2020 የበጅት ዓመት በጀት	የካቲት 2020	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት፣ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ (50%)፣ አማርኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኮሪያንኛ

*መቶኛዎች የሚያሳዩት የሁሉም የተደራሽነት ቡድን ዓባላትያንን ቋንቋ ይናገሩ እንደነበር ነው።

በሌሎች ኮንትራቶች አማካኝነት የተደገፉ ሌሎች ፕሮጀክቶችም የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ የማዳረስ ቡድን ይጠይቃሉ። የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

ተጨማሪ ፕሮጀክቶች	የጊዜ ሰሌዳ	የተደራሽነት ዓይነት	የባለ ሁለት ቋንቋ ሠራተኛ*
የማውንት ፕሌዛንት መስመር (42 ፣ 43 መስመሮች) እና የኮነቲከት አቬኑ መስመር (L1 ፣ L2 መስመሮች) የአገልግሎት ግምገማ ጥናት	ግንቦት 2018	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት፣ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ
ያውቶቡስ መለወጥ ፕሮጀችት	መስከረም-ህዳር 2018 ግንቦት 2019	በቀረበው ሀሳብ ላይ የደንበኛ ግብረመልስ ማበረታታት፣ የዳሰሳ ጥናቶችን መሰብሰብ	ስፓኒሽኛ፣ አማርኛ
የመድረክ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት በጋ 2019	ግንቦት-መስከረም 2019	ስለ ጣቢያዎች መዘጋት ለደንበኞች ማሳወቅ እና መርዳት	አማርኛ ፣ ቻይንኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ኮሪያኛ ፣ ፖርቱጋልኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL)
ሰማያዊ/ብርቱካንማ/ሲልቨር መስመር የችሎታ እና አስተማማኝነት ጥናት	ሰኔ-ሀምሌ 2019	ስለ ጥናት ለደንበኞች ማሳወቅ	ስፓኒሽኛ

ከእነዚህ ተግባራት በተጨማሪ የሜትሮ ሠራተኞች በአጠገብ ላሉት የግንባታ ፕሮጀክቶች የቋንቋ ድጋፍ ፍላጎቶች ከግምት መግባታቸውን ለማረጋገጥ እንደ ኪንግ ስትሪት - ኦልድ ታውን ሜትሮ ተደራሽነት ማሻሻያዎች ፕሮጀክት በስፓኒሽኛ እና በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሁለት የቡድን ዓባላትን ያካተተ ነበር።

በተጨማሪም፣ ሜትሮ በርካታ ለህዝብ ክፍት የሆኑ ዝግጅቶች እና የህዝብ ችሎቶች የሚያስተናግድ ሲሆን የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሠራተኞችም የሠራተኛ ዕቅዳቸው አካል ተድርገ ተካቷል። አስፈላጊ ሲሆን፣ ሜትሮ በቦታው ላይ አስተርጓሚዎች አሉት።

አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የሜትሮ የመረጃ ሰው (MIPs) በመባል የሚታወቁት የሜትሮ የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች በርካታ ተሳፋሪ የሚኖርበት ዝግጅት ወይም በጣቢያዎች መዘጋት ወቅት ደንበኞችን ይረዳሉ። የሜትሮ የመረጃ ሰው (MIPs) የምዝገባ ቅጽ ሠራተኞቹ ከእንግሊዝኛ በተጨማሪ የሚናገሯቸውን ሌሎች ቋንቋዎችን ለመዘርዘር ቦታ ያካትታል። በዚህ መረጃ ላይ መሠረት የቋንቋ ችሎታ ያላቸው MIPs አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ወይም ምንም ችሎታ ያላቸው ብዙ ሰዎች በሚገኙበት ስፍራዎች ይመደባሉ።

የጽሁፍ መገናኛ

ሜትሮ የፕሮጀክት ግንኙነቶች አካል የሆኑትን ሁሉንም አስፈላጊ ሰነዶች መተርጎሙን ይቀጥላል። እንደአስፈላጊነቱ፣ ሜትሮ በተለምዶ የሚከተሉትን ሰነዶች ለመተርጎም ጥራቱን የጠበቀ ትርጉም ይሰጣል።

- እንግሊዝኛ ባልሆኑ ጽሑፎች ውስጥ ማስታወቂያዎች
- ብሮሹሮች/አንድ መውሰድ ይቻላል ማስታወቂያዎች/በራሪ ወረቀቶች
- የፕሮጀክት ድረ-ገጾችን እና ምክሮችን፣ wmata.com የጉግል የትርጉም መሣሪያ ለቻይንኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ኮሪያኛ ፣ ስፓኒሽ እና ቬትናምኛ ቋንቋዎች እንደለው ይወቁ
- በትላልቅ ፕሮጀክቶች/ተጽዕኖዎች ብቻ ጋዜጣዊ መግለጫዎች
- የሕዝብ ችሎት ማስታወቂያዎች እና የዶኬት ሰነዶች
- ምልክቶች (ማሳወቂያ፣ የመንገድ ፍለጋ ፣ ንድፈ ሀሳቦች፣ ወዘተ…)
- የዳሰሳ ጥናቶች (በወረቀት እና በኦንላይን)

ለትላልቅ ፕሮጀክቶች የጽሑፍ ሰነዶች ብዙውን ጊዜ በመረጡት ቋንቋ ተጨማሪ መረጃን እንዴት እንደሚያገኙ በበርካታ ቋንቋዎች በአንድ መስመር ይካተታሉ።

ሜትሮ ሁሉም ሰው በአንድ ዓይነት የዕድሎች ተደራሽነት የሚጀምር አለመሆኑን በመረዳት እና አስተማማኝ ፣ ቀልጣፋ፣ ተመጣጣኝ የመጓጓዣ እጥረት መኖር ብዙውን ጊዜ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያው እድገት እንቅፋት መሆኑን በመገንዘብ ሜትሮ በዘር እና በኢኮኖሚ እኩልነት ላይ ለሚጫወተው ሚና ዝግጁ ለማድረግ “ፍታዊ የሥራ ቡድን” በ 2019 እ.አ.አ. አቋቋመ፡፡

የዚህ ቡድን የመጀመሪያ ዓላማ የወቅቱን የመጓጓዣ ፍትሃዊነትን በክልል እና በሜትሮ ደንበኛ አካባቢ ለመመዝገብ እንዲሁም በሜትሮ ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ የፍትሃዊነት ጥቅም እና አስፈላጊነትን ለማሳደግ የሚችሉ መንገዶችን ለመጠቆም ነበር፡፡ ከቡድኑ የመጀመሪያ ውጤቶች አንዱ ‘Equity Primer’ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ነፀብራቅ እና ምክር መስጫ ነበር፡፡

ሥ ል ጠ ና

የሜትሮ የታቀደውን የፕሮጀክት ግንኙነቶች ሂደት በተሳካ ሁኔታ ለማፅደቅ እና ለህዝብ ተሳትፎ የአንቀጽ 6 መስፈርቶችን በተመለከተ የባለሥልጣኑ ሰፊ ግንዛቤን ለማረጋገጥ ሠራተኞች ለፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች እና ለድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ስልጠናዎችን ይሰጣሉ።

ከ 2017 ጀምሮ ከ 100 በላይ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች እና ሠራተኞች በ PPP ስልጠና ተሳትፈዋል። በጥር 2017 እና መጋቢት 2020 መካከል አራት ሥልጠናዎች ተጠናቀዋል። የሥልጠና ቁሳቁሶች ከ “የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዱ መግቢያ” ቪዲዮ ጋር በሜትሮዌብ፣ በሜትሮ ኢንትራኔት ለሠራተኞች ይገኛሉ ፡፡

የሥልጠናዎች ማጠናቀቂያ አሁን በሜትሮ PeopleSoft Enterprise Learning Management system በኩል ተቀርጿል፣ ክትትል ተደርጓል እና ሪፖርት ተደርጓል።.

ክፍለ ጊዜ	የሳታፊዎች ቁጥር	አጀንዳ	የግብረ-መልስ ውጤቶች
የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ መግቢያ *የካቲት 27, 2018* Jackson Graham Building 600 5th St NW, Washington DC	25 የፕሮጀክት አስተዳዳሪዎች እና ሌሎች ሠራተኞች ከግንኙነት እና ተደራሽነት ሠራተኞች ጋር የተያያዙ	• የተሳትፎ እቅድ ቪዲዮ መግቢያ • ተጽዕኖ የደረሰበትን ህዝብ መገንዘብ • የታቀዱ የፕሮጀክት ግንኙነቶች እና ተደራሽነት መመሪያዎች	• 25% የሚሆኑት እንዳልተሰማቸው ወይምከስልጠናው በፊት PPP ን በተወሰነ መልኩ ተረድቷል፡፡ • 80% የሚሆኑት PPP ን በጣም እንደተገነዘቡ ወይም ከስልጠናው በኋላ የበለጠ አዋቂ እንደሆኑ ተሰማቸው፡፡ • 94.74% የሚሆኑት ጊዜያቸውን በአግባቡ እንደተጠቀሙበት ተሰማቸው፡፡ *የመሻሻል አስተያየቶች ተጨማሪ ምሳሌዎች:*
የህዝብ ተሳትፊ አስተዳደር ዘዴ (PPMS) *የካቲት 28 እና መጋቢት 6, 2018* Jackson Graham Building 600 5th St NW, Washington DC (computer lab) *መጋቢት 2, 2018* Carmen Turner Facility 3500 Pennsy Drive Hyattsville, MD (የኮምፒውተር ላብ)	14 የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች ወይም የመምሪያ ተወካዮች	• በ PPMS ውስጥ የተጠቃሚ ሚናዎች • የስርዓት አጠቃላይ እይታ • የሥልጠና አካባቢ • አዲስ የፕሮጀክት ግብዓት (ልምምድ)	• 34% የሚሆኑት ከስልጠናው በፊት ስለ PPMS በጭራሽ ወይም በመጠኑ ያውቃሉ፡፡ • 79% የሚሆኑት PPMS ን ብዙ እንደተረዱ ወይም ከስልጠናው በኋላ ዐዋቂ እንደሆኑ ተሰማቸው፡፡ • 100% ጊዜያቸውን በአግባቡ እንደተጠቀሙበት ተሰማቸው፡፡ *የመሻሻል አስተያየቶች* *በእያንዳንዱ PPMS ስርዓት ተጨማሪ ጊዜ*
የሕዝባዊ ተሳትፎ ዕቅድ መግቢያ *ታህሥ 13, 2019* Jackson Graham Building 600 5th St NW Washington DC	ከግንኙነት እና ከማዳረስ ጋር የተያያዙ 45 የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች እና ሌሎች ሠራተኞች	• ለህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ መግቢያ ቪዲዮ • ተጽዕኖ ያደረሰበትን ሕዝብ መረዳት • የታቀዱ የፕሮጀክት ግንኙነቶች እና ተደራሽነት መመሪያዎች	• 71% የሚሆኑት ከስልጠናው በፊት ስለ PPMS በጭራሽ ወይም በመጠኑ ያውቃሉ፡፡ • 81% የሚሆኑት PPP ን በጣም እንደተገነዘቡ ወይም ከስልጠናው በኋላ ዐዋቂ እንደሆኑ ተሰማቸው፡፡ • 100% ጊዜያቸውን በአግባቡ እንደተጠቀሙበት ተሰማቸው፡፡ *የመሻሻል አስተያየቶች፣ተጨማሪ ምሳሌዎች፣ በእውነተኛ ፕሮጀክት ሂደት ማሳየት*
በምርምር አውደ ጥናት የደንበኞችን ባህሪ ለይቶ ማወቅ *ታህሳስ 13, 2019* Jackson Graham Building 600 5th St NW Washington DC	32 የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች እና ከመገናኛ እና ከማዳረስ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሠራተኞች	• የጉዳይ ጥናት ሥራ • የንግድ ጥያቄዎችን ማዳበር • ለምርምር የሚሆኑ ጥያቄዎችን ለይቶ ማወቅ • ለምርምር ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚያስፈልጉ የመረጃ ዓይነቶች	አይመለከተውም

የሠራተኞች አወቃቀር

በሜትሮ ታሪካዊ የካፒታል መርሃግብር እድገት እና በፖሊሲ፣ በዕቅድ፣ በግንባታ/ጥገና፣ በጋራ ልማት እና በአጠገብ ግንባታ ዙሪያ ያሉ ፕሮጀክቶችና ተነሳሽነቶች በመጨመሩ ፍላጎትን ለማርካት በጋራ መልሶ ማዋቀር እና ማስፋፋት አስፈላጊ ነበር፡፡ የግንኙነት ፕሮጀክት አስተዳደርን፣ የይዘት ግንባታን እና የተደራሽነት ፕሮግራሞችን ለማቅረብ ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የትብብር ግንኙነቶችን ለማዳበር እና ከሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ እና ከ FTA መስፈርቶች ጋር መጣጣምን ለማረጋገጥ አንድ አዲስ የይዘት እና ስትራቴጂ ግንኙነቶች ጽህፈት ቤት በመጋቢት 2020 ተመሠረተ፡፡ ከሰኔ 2020 ጀምሮ የሚከተሉት ተጨማሪ የሠራተኛ ድጋፍ ቦታዎች፤ የታቀዱ የፕሮጀክት ግንኙነቶች እና ተሳትፎ ዲሬክተር፣ የስትራቴጂ ግኙነት ሥራ አስኪያጆች፣ አንድ የተደራሽነት ሥራ አስኪያጅ እና የይዘት ስቱዲዮ ሥራ አስኪያጅን ያካትታሉ፡፡

ቡድኑ ፕሮጀክቶችን ለማስተባበር እና ተገዢነትን ለማረጋገጥ በኤጀንሲው ውስጥ ካሉ ሌሎች ጽ/ቤቶች ጋር በቅርበት መስራቱን ቀጥሏል፡፡ ቡድኑ በመጪው ፕሮጄክቶች ላይ ለመወያየት እና የግንኙነት ስልቶችን እና ታክቲኮችን በመደበኛነት ለማሻሻል ከደንበኞች ምርምር ቢሮዎች፣ የደንበኞች አገልግሎት፣ ከመንግሥት ግንኙነቶች፣ ማርኬቲንግ እና የሚድያ ግኑነቶች ተወካዮች ጋር ስብሰባ ያደርጋል፡፡ ቡድኑ በየሳምንቱ ከሌሎች አጋር ቢሮዎች - የ ADA ፖሊሲ እና እቅድ ቢሮዎች ፣ የደንበኞች ምርምር ፣ የእኩል የሥራ ስምሪት ዕድል እና የዕቅድ ዝግጅት ጽህፈት ቤቶች - የወቅቱን እና መጪዎቹን ፕሮጀክቶች የስነ-ህዝብ እና የአንቀስ 6 ተገዢነትን ለማረጋገጥ ይሰበሰባል፡፡

ከአዲሱ ሁኔታ ጋር መለማመድ

ዓለም በኮቪድ -19 ለተፈጠረው ወረርሽኝ ምላሽ መስጠቱን እንደቀጠለ፣ ሜትሮ የወደፊቱ የግንኙነቶች እና የህዝብ ተሳትፎ ምን ሊመስል እንደሚችል እንደገና እያሰላሰለ ነው፡፡ በአካል በተደረጉ ብዙ ግንኙነቶችም ሆነ ለህዝብ ክፍት በሆኑ ዝግጅቶች ዙሪያ በተደረጉ ብዙ ቀደምት የተደራሽነት ስኬቶች ፣ ሜትሮ የተጠቃሚዎቹን የማያሳተፉ እና የሚጠብቁ አዳዲስ ዘዴዎችን እና ስትራቴጂዎችን ማስፋፋት አለበት፡፡

ሜትሮ ወደ ኦንላይን ስብሰባዎች ከመሸጋገሩ በተጨማሪ በወረርሽኝ የመጀመሪያዎቹ ወራት የደንበኞቹን እና የተደራሽነት ቡድኖቹን ደህንነት እየጠበቀ በአካል የደንበኛ ማስታወቂያን ለመቀጠል የተጠበቀ የመረጃ ቋት በፍጥነት አሰማርቷል፡፡ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በተከሰተው ታሪካዊ ዝቅተኛ የተሳፋሪ ቁጥር ምክንያት ሜትሮ በየሰዓቱ የሚካሄድ ጥሩ የጥገና ሥራ ጥረቶችን በማካሄድ በሳምንት ከአንድ እስከ አራት ጣቢያዎችን መዝጋት ተችሏል፡፡ የደንበኞች ተደራሽ ቡድኖች በፕላስቲክ የተከበቡ አዳዲስ የመረጃ ቋቶችን፣ በርካታ የበራሪ ወረቀት ማስቀመጫዎችን እና በአካላዊ ግንኙነቶች ላይ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ በመስጠት አካላዊ ግንኙነቶችን ለመገደብ የሚረዱ ትልልቅ QR ኮዶች ያላቸው ምልክቶችን ይጠቀሙ ነበር፡፡ እነዚህ ቋቶች በየጠዋቱ ተተክለው በእያንዳንዱ ቀን መጨረሻ ለማፅዳት ይወርዳሉ፡፡ ቋቶቹ ተጽዕኖ በደረሰባቸው ጣቢያዎች ከመዘጋታቸው አንድ ሳምንት በፊት ይተከላሉ፡፡ ሌሎች የተደራሽ ቡድኖች ጣቢያው በተዘጋበት ጊዜ አቅጣጫዎችን እና የሻትል አውቶቡስ ጥያቄዎችን ለመመልስ በጣቢያዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡

በአባሪ ሐ: የአቻ ትራንዚት ኤጄንሲ ግምገማ ላይ እንደተጠቀሰው እንደ ብዙዎቹ የአቻ ትራንስፖርት ኤጀንሲዎች፣ ሜትሮ መገናኛ ሰነዶችን በማሰራጨት፣ ስብሰባዎችን ወይም ዝግጅቶችን በማካሄድ እና ግብረመልሶችን ለመሰብሰብ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ተጨማሪ መንገዶችን እያሰላሰለ ነው፡፡ በተለይ ለመድረስ አስቸጋሪ የሆኑ የሜትሮ ደንበኞችን እና የማህበረሰብ ዓባላትን ለመድረስ ተገቢዎቹን የማሰራጫ ዜዴዎች በመወሰን ረገድ የሜትሮ ደንበኞች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡